# የመልክዓምድር እሳቤ እና አዕምሯዊ ውክልና፤ በድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ

ሰሎሞን ተሾመ[1] እና ታደሰ በሪሶ[2]

**አጠቃሎ**

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ መልክዓምድር በአዕምሯዊ ውክልና ውስጥ ያለውን እሳቤ መመርመር ነው። ጥናቱ በኦሮሚያ ክልል፣ በባሌ ዞን፣ በጎሎልቻ ወረዳ፣ በአናጂና ቀበሌ ውስጥ በሚገኘው የድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ ላይ ያተኮረ ነው። ጥናቱ አይነታዊ የምርምር ስልትን የተከተለ ሲሆን፤ ምልከታ፣ ቃለመጠይቅና የንጥል ሁነት ማሳያ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎችን ተግባራዊ አድርጓል። የተሰበሰቡት መረጃዎች ያላቸውን ትርጉም በፍከራ ለመመርመር የኮግኒቲቭ ንድፈ ሃሳብ ዘርፍ የሆነው አዕምሯዊ ካርታ አስተሳሰብ ጥቅም ላይ ውሏል።[3] በጥናቱም የድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ መገኛ ቦታ ስያሜ፣ የቦታው ቅዱስነት እሳቤ፣ ሰው ሰራሽ ግንባታዎች፣ ተፈጥሯዊ ገጽታዎች፣ እንዲሁም በመልካነ ቅርሱና በሼኽ ሁሴን ባህርያት መካከል ያለው እሳቤያዊ ትስስር በሼኽ ሁሴን ተከታዮች ዘንድ የፈጠሩትን አዕምሯዊ ውክልና ተዳሷል። በመልክዓምድራዊ ገጽታዎቹ መሰረት ስፍራው ያለው አዕምሯዊ ውክልና በአምላክ ምርጫ የተመሰረተ ቅዱስ ስፍራ፣ የምድር እምብርት፣ የሕዋ ማዕከልና ከምድር በታች፣ በምድር ላይና ከምድር በላይ ያሉ አካላትን የሚያገናኝ እንደሆነ ጥናቱ አመላክቷል። ይህም በመሆኑ ስፍራው ግለሰብን፣ ማህበረሰብን፣ ሼኽ ሁሴንን እና ፈጣሪን በአንድ በማገናኘት የአራትዮሽ ትስስር የፈጠረ ተደርጎ እንዲታሰብ ምክንያት ሆኗል። ከአዕምሯዊ ውክልና አንጻር በስፍራው የሚገኙ መልክዓምድራዊ ገጽታዎች ምድርን፣ ከምድር በታች ያለን አካልና ከምድር በላይ ያለን አካል የሚያገናኙ የምድራዊና የሰማያዊ ጀነት (ገነት) አምሳያዎች እንደሆኑ ጥናቱ አመላክቷል።

**ቁልፍ ቃላት፤** *መልክዓምድር፣ ኮግኒቲቭ፣ አዕምሯዊ ውክልና፣ ትዕምርት*

[1] የፎክሎር ጥናት ትምህርት ክፍል፣ ባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ

[2] የኢትዮጵያ ጥናት እና ምርምር ተቋም፣አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

[3] የኮግኒቲቭ ንድፈሃሳብ የአስተሳሰብ ሂደቶችን በመረዳት የሰው ልጅን ባህርይ ወይም ጸባይ የሚተነትን የስነልቡና (Psychology) ንድፈሃሳብ አካል ነው።

## 1. የጥናቱ ዳራ

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ የድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ (Shrine) ያለውን መልክዓምድራዊ እሳቤና አዕምሯዊ ውክልና መመርመር ነው። 'Shrine' የሚለው የእንግሊዘኛ ቃል በአረብኛ 'ማዛር' በሚል ይተረጎማል። ይህን ቃል በአማርኛ በትክክል የሚገልጽ ቃል አልተገኘም። በመሆኑም በዚህ ጥናት ለእሳቤው አቻ ይሆናል በሚል 'መካነ ቅርስ' የሚለው ቃል ጥቅም ላይ ውሏል።

'መካነ ቅርስ' ከነብያት፣ ከቅዱሳን ወይም ከፈጣሪ ወዳጆች ጋር ተያይዞ የሚገነባ ኪነህንጻን ወይም ኪነህንጻዎች የሚገኙበት ስፍራን የሚገልጽ ሲሆን፣ መንፈሳዊ ተጓዦች ወደ ስፍራዎቹ በመሄድ ነብያትን፣ ቅዱሳንን ወይም የፈጣሪ ወዳጆችን እንደሚዘይሩ (እንደሚጎበኙ) Renard (2009፣ 221) ይገልጻል።

የድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ በ12ኛው መቶ ክ/ዘመን እንደተመሰረተ የሚነገር ተፈጥሯዊ፣ ኃይማኖታዊ፣ ባህላዊና ታሪካዊ ስፍራ ነው። መካነ ቅርሱ በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት፣ በባሌ ዞን፣ በጎሎልቻ ወረዳ፣ በአናጂና ቀበሌ ውስጥ ይገኛል። የአናጂና ቀበሌ ከአዲስ አበባ በደቡብ ምስራቅ አቅጣጫ በ 610 ኪ.ሜትር ርቀት ላይ ሲገኝ፣ ከባሌ ዞን ዋና ከተማ ሮቤ ደግሞ በ 180 ኪ.ሜትር ርቀት ላይ ይገኛል።

ስፍራው ስያሜውን ያገኘው መካነ ቅርሱን በመሰረቱት በሼኽ ሁሴን ሼኽ ኢብራሂም ስም ነው። ሼኽ ሁሴን በተከታዮቻቸው ዘንድ እጅግ የተከበሩ ትልቅ መንፈሳዊ አባት፣ ከፈጣሪ ጋር ባላቸው ልዩ ቅርበት ሰውን ከፈጣሪ ጋር የሚያገናኙ፣ የፈጣሪ መልዕክተኛ፣ የፈጣሪ ባርያ፣ ፈጣሪ ልመናቸውን የሚሰማ፣ በእሳቸው ስም የሚለምን ማንኛውም ሰው እንደሚሳካለት፣ በማንኛውም ሰዓት ለጠራቸው ሰው ፈጥነው እንደሚደርሱ፣ በየትኛውም ስፍራ እንደሚገኙ፣ በጭንቀት ወቅት ስማቸውን ጠርቶ ድረሱልኝ ላለ ሰው ሁሉ ፈጥኖ ደራሽ እንደሆኑ ይታመንባቸዋል።

ሼኽ ሁሴን የነብዩ መሃመድ የአጎት ልጅ ከሆኑት አቂል- ኢብን- አቢ-ጣሊብ የዘር ሀረግ 12ኛ ትውልድ እንደሆኑ Andrzejewski (1972) እና Eshetu (1973) ይገልጻሉ። የሼኽ ሁሴን አባት ሼኽ ኢብራሂም ሲሆኑ እናታቸው ሸምሲያ ይባላሉ። ቤተሰባቸውን በሚመለከት የተለያዩ መረጃዎች አሉ። Braukämper (2004፣ 132) ከዛሬ 800 ዓመት በፊት የሼኽ ሁሴን አያት የሆኑት ሰዒድ አብደላህ ከአረቢያ በሱማሊያ በኩል አድርገው ወደ አናጂና እንደመጡ ይገልጻል።

ሼኽ ኢብራሂምና ባለቤታቸው ሸምሲያ ከየመን አገር ተነስተው በሱማሊያ-መርካ በኩል ወደ ባሌ እንደመጡ፣ ከየመን የወጡትም በጠብ ምክንያት

እንደሆነ መረጃ ሰጪዎች ይገልጻሉ፡፡ የጠቡ መንስኤም ሸምሲያ ከቀድሞ ባለቤታቸው ጋር ከተፋቱ በኋላ ሼኽ ኢብራሂምን አግብተው ሲኖሩ የቀድሞ ባለቤታቸው 'የእኔን ልጅ ነው ያረገዘችው'፣ ስለዚህ ሌላ ባል ማግባት አትችልም' በማለታቸው ጠብ ተፈጠረ፡፡ በዚህ ምክንያት ሀገራቸውን ጥለው ባሌ በመምጣት መኖር ጀመሩ ተብሎ ይነገራል፡፡

አንዳንድ ምሁራን ግን የሼኽ ሁሴን ቤተሰቦች ሳይሆኑ እራሳቸው ሼኽ ሁሴን ከኢራቅ ባግዳድ ከተማ ተነስተው በሐረር በኩል ወደ ስፍራው መምጣታቸውን ይገልጻሉ (Smith 1896፣ 125 እና Cerulli 1922፣ 152) ፡፡ ይሁን እንጂ በዚህ ጥናት ውስጥ የተሳተፉ መረጃ ሰጪዎች በሙሉ የሼኽ ሁሴን እናትና አባት ከውጭ አገር እንደመጡ፣ እንዲሁም ሼኽ ሁሴን የተወለዱትና ያደጉት ባሌ ዞን አናጂና ቀበሌ እንደሆነ ይስማማሉ፡፡

የሼኽ ሁሴንን የትውልድ ዘመን በተመለከተ የተለያዩ መረጃዎች አሉ፡፡ Gemechu (2013) በ9ኛው መቶ ክ/ ዘመን መጨረሻ እንደተወለዱ ሲገልጽ Andrzejewski (1975) በበኩሉ በ12ኛው መቶ ክ/ ዘመን እንደተወለዱ ይገልጻል፡፡ Areba, Abel እና Ibrahim (2003) በ11ኛው መቶ ክ/ዘመን መጨረሻ እንደተወለዱ ሲገልጹ Eshetu (1973)፣ Lewis (1977)፣ Mohamed (1990)፣ Temam (2002) እና Braukämper (2004) ደግሞ ሼኽ ሁሴን በ12ኛው እና በ13ኛው መቶ ክ/ዘመን መካከል የኖሩ መሆናቸውን ይገልጻሉ፡፡

በጥናቱ የተሳተፉ መረጃ ሰጪዎች ሼኽ ሁሴን መቼ እንደተወለዱ ሁለት መረጃዎችን አቅርበዋል፡፡ አንደኛው፤ ከዛሬ 950 አመት በፊት እንደተወለዱ የሚገልጽ ነው፡፡ ይህ ደግሞ በ1057 ዓ.ም አካባቢ ማለት ነው፡፡ ሁለተኛው፤ በነብዩ መሀመድ እና በሼኽ ሁሴን ውልደት መካከል 5 ቀርን መኖሩን የሚገልጽ ነው፡፡ ቀርን የሚለው ቃል አረብኛ ሲሆን፣ ትርጉሙም ክፍለ ዘመን ማለት ነው፡፡ 1 ቀርን 100 ዓመት ነው፡፡ በመሆኑም በሼኽ ሁሴንና በነብዩ መሃመድ መካከል የ500 ዓመት ልዩነት አለ፡፡

ነብዩ መሃመድ የተወለዱት እ.አ.አ በ570 አካባቢ ነው (Gulevich 2004፣ 57)። በዚህ ስሌት መሰረት ሼኽ ሁሴን የተወለዱት በ12ኛው መቶ ክ/ዘመን መጀመሪያ ላይ እ.አ.አ በ1070 ወይም በ1062 ዓ.ም አካባቢ ማለት ነው፡፡ የሼኽ ሁሴንን የውልደት ዘመን አስመልክቶ ከቀረቡት መረጃዎች መካከል በ12ኛው መቶ ክ/ዘመን መጀመሪያ ላይ መኖራቸውን የሚገልጸው በተሻለ አሳማኝ ይመስላል፡፡

## 2. ጽንሰ ሃሳባዊ እና ንድፈ ሃሳባዊ ዳሰሳ

የኮግኒቲቭ ንድፈ ሃሳብ በሰው ልጅ አዕምሮ (Mind) ላይ ትኩረት የሚያደርግ የስነልቡና (Psychology) ንድፈ ሃሳብ አካል ሲሆን፣ በ1970ዎቹ መተዋወቅ የጀመረ ነው። የኮግኒቲቭ ንድፈሃሳብ የአስተሳሰብ ሂደቶችን በመረዳት የሰው ልጅን ባህርይ ወይም ጸባይ የሚተነትን ነው። ይህ ንድፈ ሃሳብ በስሩ የተለያዩ ዘርፎች ያሉት ሲሆን የሰው ልጅ አዕምሮ ከኃይማኖት ጋር ያለውን ትስስር የሚያጠናው ዘርፍ "የኃይማኖት ኮግኒቲቭ ሳይንስ" (cognitive science of religion) ይሰኛል (Andresen 2001)።

ይህ ዘርፍ የሰው ልጅን ኮግኒቲቫዊ ሁነቶች ካለው የኃይማኖት ተመክሮ፣ ኃይማኖታዊ ባህርያት፣ እምነት፣ ኃይማኖታዊ ስርዓት፣ ቅዱስ ናቸው ብሎ ከሚያምንባቸው ስፍራዎች፣ ልዩ መለኮታዊ ኃይል አላቸው ብሎ ከሚያምንባቸው ቁሶችና ከሌሎች እሴቶች ጋር በማገናኘት በአዕምሮ ውስጥ በሚፈጥረው ትዕምርት ላይ የሚያተኩር ነው (Beit-Hallahmi እና Argyle 1997፣ 81-84)። የአስተሳሰቡ ዋና ትኩረት የሰው ልጅ ኃይማኖታዊ እሳቤዎችን ወይም ቁሶችን በሚመለከት ያለውን አዕምሯዊ ውክልና (Mental representation) መመርመር ነው።

የአዕምሯዊ ውክልና መሰረት የሚያደርገው በእሳቤዎቹ ላይ ያለውን የጋራ ግንዛቤ፣ እምነት፣ ተግባራት፣ ስርዓታዊ ገጽታና የጋራ ገለጻ ላይ ነው (McCauley 2010፣782)። ይህ የተለያዩ ግለሰቦች አዕምሮ ውስጥ የሚኖረው ውክልና ሲደጋገምና በቡድን ውስጥ ሲስፋፋ የባህል ውክልና (cultural reperesentation) ይሆናል። ይህን የግለሰቦች አዕምሯዊ ውክልና ወደ ባህል ውክልና መለወጥን የሚያጠና የኃይማኖት ኮግኒቲቭ ሳይንስ ዘርፍ "ኢፒዲሞሎጂካል ፈለግ" (Epidemiological Approach) ይሰኛል (Sperber 1990)።

ይህ ጥናትም ኢፒዲሞሎጂያዊ ፈለግን መነሻ በማድረግ የኮግኒቲቭ ሳይንስና ባህል ያላቸውን ትስስር ከመልክዓምድር (Geography) አንጻር ይመረምራል። በኮግኒቲቭ ንድፈ ሃሳብ መሰረት መልክዓምድር ላይ ያሉትን ልዩ ልዩ ምልክቶች በአዕምሮ ውስጥ በማስገባት ትርጉም እንዲይዙና ለማህበረሰባዊ የጋራ እሳቤዎች መፈጠር እንደሚረዱ የሚያቀነቅነው ዘርፍ "የአዕምሯዊ ካርታ" አስተሳሰብ ("Mental map" school) ተብሎ ይታወቃል (Fickeler 1962)። በዚህ አስተሳሰብ መሰረት መልክዓምድር በሰው አዕምሮ ውስጥ ትርጉም ያለውና የሰው ልጅ ወደ ጎንና ወደ ላይ የሚኖረውን ግንኙነት የሚወስን እንዲሁም የጋራ ማህበራዊ እሳቤዎችን የሚፈጥር ነው።

መልክዓምድርና ኃይማኖት ያላቸውን የእርስበርስ ትስስር በኃይማኖት ጥናት ውስጥ መመልከት እምብዛም አልተለመደም፡፡ ይሁንና መልክዓምድር ለኃይማኖት ጥናት መሰረታዊ ምልክት (code) እንደሆነ Isaac (1959) እና Fickeler (1962) ይገልጻሉ፡፡ የኃይማኖት እሳቤ፣ የቅዱስነት እሳቤ፣ የኃይማኖት ታሪክና በኃይማኖቱ ውስጥ የተፈጸሙ ገድላት በቀጥታ ከመልክዓምድር ጋር የተቆራኙ ናቸው፡፡ ኃይማኖታዊ መሰረት ያለው መልክዓምድር ከቅዱስነት፣ ከልዩ ክብርና ከፍጹምነት ጋር የተያያዘ ነው (Francaviglia 2003፣ xxi)፡፡ ይህ ስፍራ ከሌሎች ስፍራዎች በተለየ መንፈሳዊ የመልክዓምድር እሳቤን (Spritual geography) የያዘ፣ በሰው አዕምሮ ውስጥ ልዩ ትርጉም ያለውና የሰው ልጅ ወደ ጎንና ወደ ላይ የሚኖረውን ግንኙነት የሚወስን ነው (Fickeler 1962)፡፡

መልክዓምድር ባለው ልዩ ኃይማኖታዊና ማህበራዊ ደረጃ፣ በስፍራው በሚገኙ ተፈጥሯዊ ሁነቶችና ሰው ሰራሽ ግንባታዎች፣ ስለስፍራው በሚነገሩ አፈታሪኮች፣ ልዩ ምልክቶችና ስፍራው ላይ አለ ተብሎ በሚታመን ልዩ ኃይል መነሻነት እንደ መጽሐፍ (text) የሚነበብና መልዕክት የሚያስተላልፍ ነው (Fickeler 1962)፡፡ መልክዓምድር ምልክት ሆኖ ትርጉም የሚሰጠው በማይታየውና በማይጨበጠው ህዋዊ ዓለም (universe) ውስጥ ያለን ምናባዊ እሳቤ፣ በሚታየው ዓለም ውስጥ ካለ ተጨባጭ እሳቤ ጋር በኮግኒቲቭ በማገናኘት ነው፡፡

እነዚህ ሁለት እሳቤዎች በኮግኒቲቭ የሚገናኙት ሶስት የማወቂያ ስርዓታዊ ሂደቶችን በማለፍ እንደሆነ Ardalan እና Bakhtiar (1973፣10) Corbin (1960)ን በመጥቀስ ተከታዩን ሀሳብ አስፍረዋል፡፡ "ምናባዊ ቁስ አካል" (Immaterial matter) ወደ "እሳቤያዊ የውክልና ስዕል" (Archetypal figure) ይቀየራል፡፡ "እሳቤያዊ የውክልና ስዕል" ደግሞ ወደ "ምናባዊ ስዕል" (Idea-Image) ይቀየራል፡፡ እነዚህ ሂደቶች የሚቀየሩትም በአንድ መልክዓምድር ላይ በሚገኙ ትዕምርቶች (symbols) አማካኝነት ነው፡፡

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ መልክዓምድር በአዕምሯዊ ውክልና ውስጥ ያለውን እሳቤ መመርመር ነው፡፡ የመካነ ቅርሱ መገኛ መልክዓምድር ያለውን አዕምሯዊ ውክልና ለመመርመር የቦታው ስያሜ፣ በስፍራው የሚገኙ ተፈጥሯዊ ሁነቶች፣ ሰው ሰራሽ ግንባታዎች፣ ልዩ ልዩ ምልክቶች፣ በቦታው ላይ የሚነገሩ አፈታሪኮች፣ ከቦታው ጋር በተያያዘ በሼኽ ሁሴን ላይ የሚነገሩ ሚቶሎጂያዊ ትረካዎች እንዲሁም የሼኽ ሁሴን ተከታዮች በቦታውና በሼኽ ሁሴን ላይ ያላቸው ልዩ እምነት መነሻ ሆነዋል፡፡

## 3. የአጠናን ዘዴ

ይህ ጥናት አይነታዊ የምርምር ንድፍን የተከተለ ሲሆን ለጥናቱ ጠቃሚ የሆኑ ቀዳማይና ካልዓይ መረጃዎች ተሰብስበዋል፡፡ ቀዳማይ መረጃዎች የሚሰበሰቡት ከመስክ ስራ (Field work) ነው፡፡ በመስክ ስራ ወቅት መረጃዎች የሚሰበሰቡት በምልከታና ቃለመጠይቅ እንደሆነ Goldstein (1964፣77) ይገልጻል፡፡ ከእነዚህ ዘዴዎች በተጨማሪ የንጥል ሁነት ማሳያ (Case study) አንዱ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ መሆኑን Bloor እና Wood (2006፣27) ይገልጻሉ፡፡ ይህ ጥናት እነዚህን ሶስት የመስክ መረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች ተጠቅሟል፡፡

Kothari (2004፣96) ምልከታ የተደራጀ (Structured) እና ያልተደራጀ (Unstructured) በሚሉ ሁለት አይነት ስልቶች እንደሚመደብ ይገልጻል፡፡ የዚህ ጥናት ንድፍ አይነታዊ በመሆኑ የተደራጀ ምልከታን ተግባራዊ አድርጓል፡፡ የተደራጀ ምልከታ በሶስት መንገድ እንደሚካሄድ Kothari (2004፣ 96) ይገልጻል፡፡ እነሱም፡- አጥኚው በመስክ ላይ የሚከወኑ ድርጊቶችን በጋር እየተገበረ ምልከታ የሚያደረግበት ተሳታፊ ምልከታ፣ አጥኚው ከዋኞቹ የሚከውኗቸውን ድርጊቶች ሳይከውን ምልከታ ብቻ የሚያደርግበትና ከዋኞቹ ድርጊቶችን በሚከውኑበት ወቅት አጥኚው በስፍራው ስለመኖሩ ፍንጭ ሳይሰጥና ከዋኞቹ ሳያውቁ በድብቅ ምልከታ የሚያደርግበት ናቸው፡፡ እነዚህ ሶስት የምልከታ መንገዶች በጥናቱ ወቅት ተግባራዊ ተደርገዋል፡፡

ምልከታ የሚካሄድባቸው አውዶች በተለያዩ መንገዶች ሊገኙ ይችላሉ፡፡ እነዚህን አውዶች Goldstein (1974፣81-82) ተፈጥሯዊና 'አርቲፊሻል' በሚል በሁለት ሲመድባቸው፤ ፈቃደ (1991 ዓ.ም ፣122-124) ደግሞ በእነዚህ ሁለት ምደባዎች ላይ ቅንብር ተፈጥሯዊ (Induced natural) የሚል አውድ በመጨመር በሶስት ይከፍላቸዋል፡፡ በዚህ ጥናት ምልከታ የተካሄደው በመካነ ቅርሱ በሚከበሩ የ'ኢድ-አል-አድሃ' (አረፋ) እና የ'ዛህራ ገልገላ ጎበና' በዓላት ወቅት በስፍራው በመገኘት በተፈጥሯዊ የምልከታ አውድ ነው፡፡ የመስክ ስራው የተከናወነው በሁለት ዙር ለ 12 ቀናት ነው፡፡ አንደኛው ዙር፣ ከመጋቢት 25 እስከ ሚያዝያ 1 ቀን 2008 ዓ.ም ሲሆን፣ ሁለተኛው ዙር ደግሞ ከነሐሴ 25 እስከ ጳቅሜ 1 ቀን 2009 ዓ.ም ነው፡፡

በምልከታ ከተሰበሰቡ መረጃዎች መካከል ዋናዎቹ መንፈሳዊ ተጓዦች በመካነ ቅርሱ ቅጽር ግቢ ሲደርሱ የሚፈጠርባቸው የስሜት ለውጥ፣ የሚያደርጉት የሰውነት እንቅስቃሴ፣ በቅጽር ግቢው በሚገኙ ተፈጥሯዊና ሰው ሰራሽ ኪነ-ህንጻዎች አካባቢ የሚፈጽሟቸው ድርጊቶች ናቸው፡፡ በምልከታ የተገኙ መረጃዎችም በቪዲዮ ካሜራ፣ በፎቶ ግራፍ፣ በመቅረጸ-ድምጽና በማስታወሻ ደብተር ተሰንደዋል፡፡

ቃለመጠይቅ የተደራጀ (Structured) እና ያልተደራጀ (Unstructured) በሚሉ ሁለት አይነት ስልቶች እንደሚዋቀር Kothari (2004፣98) ይገልጻል፡፡ በዚህ ጥናት ያልተደራጀ የቃለመጠይቅ ስልትን መሰረት በማድረግ መረጃ ተሰብስቧል፡፡ በጥናቱ ላይ የተሳተፉ መረጃ ሰጪዎች ብዛት 11 ናቸው፡፡ በቃለመጠይቅ ከተሰበሰቡ መረጃዎች መካከል የሼኽ ሁሴን ታሪክ፣ ሼኽ ሁሴን ፈጽመዋቸዋል ተብለው የሚታመኑ ተዓምራት፣ በመካነ ቅርሱ የሚገኙ ኪነህንጻዎች ታሪክ፣ መንፈሳዊ ተጓዦች ለስፍራው ያላቸው አመለካከት፣ የስፍራውን ቅዱስነት የሚገልጹበት ደረጃ፣ ለስፍራው ያላቸውን ልዩ ክብር፣ ከስፍራው ጋር ያላቸው ግንኙነትና መሰል ጉዳዮች ናቸው፡፡

ይህ ጥናት ከምልከታና ከቃለመጠይቅ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች በተጨማሪ የንጥል ሁነት ማሳያ ዘዴን ተጠቅሟል፡፡ የንጥል ሁነት ማሳያ ዘዴ አንድ የመረጃ መሰብሰቢያ ስልት ሲሆን፣ በነጠላ ወይም አነስተኛ ቁጥር ባለው ተፈጥሯዊ መቼት አማካኝነት ማህበራዊ ሁነቶችን በጥልቀት ለመረዳት የሚጠቅም ነው (Bloor እና Wood 2006፣27)፡፡ ይህ ዘዴም ጥቂት ግለሰቦችን፣ ቡድኖችን፣ ድርጊቶችን፣ የክወና አንጓዎችን (Episodes)፣ ሁነቶችን፣ ውስን ቦታዎችን ወዘተ. መሰረት በማድረግ በተወሰነ ርዕሰ ጉዳይ ላይ ጥልቅ መረጃ ለማግኘት፣ ውስን መረጃዎች ያላቸውን ልዩነቶችና ተመሳስሎ እንዲሁም ያላቸውን ሕብርና አጠቃላይነት በጥልቀትና በስፋት ለመረዳት ይጠቅማል፡፡

ጥናቱ የንጥል ሁነት ማሳያ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴን መሰረት በማድረግ በስፍራው የተገኙ ሰዎች ለምን እንደመጡ፣ የግለሰቦች ልዩ የህይወት ገጠመኞች፣ እንዴት ወደ ስፍራው መምጣት እንደጀመሩ፣ መንፈሳዊ ቦታው የግል ችግራቸውን እንዴት እንደፈታላቸው፣ በሼኽ ሁሴንና በመካነ ቅርሱ ላይ ያላቸው እሳቤ ምን እንደሆነና መሰል ጉዳዮችን መርምሯል፡፡ በዚህ ዘዴ አማካኝነት መካነ ቅርሱ የሚገኝበትን ስፍራ፣ ሰው ሰራሽ ግንባታዎችንና ተፈጥሯዊ ሁነቶችን በተናጠል በመውሰድ ያላቸውን ልዩ ባህርይ ለመተንተን ጥረት ተደርጓል፡፡

# 4. የድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ መልክዓምድራዊ እሳቤ እና አዕምሯዊ ውክልና

## 4.1 የቦታው ስያሜ እና አዕምሯዊ ውክልና

የድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ የሚገኝበት ቦታ ድሬ፣ አናጂና እና ቢርካ በሚሉ ስያሜዎች ይታወቃል፡፡ ከእነዚህ ሶስት ስሞች መካከል በስፋት የተለመደው ድሬ የሚለው ነው፡፡ ስፍራው 'ድሬ' የሚለውን ስያሜ እንዴት እንዳገኘ የሚነገሩ ሁለት መላምቶች አሉ፡፡ አንደኛው፣ በኦሮምኛ 'ድሬ' ሜዳማ መሬት ማለት ነው፡፡ በመሆኑም ድሬ ሼኽ ሁሴን የሚለው ስያሜ የሼኽ ሁሴን ሜዳማ መሬት የሚል ትርጉም አለው፡፡

ሁለተኛው፣ ደግሞ ሼኽ ሁሴን ስፍራውን የኃይማኖት ማዕከል ከማድረጋቸው በፊት ድሬ የሚባል ሰው ይኖርበት ነበር፤ ቦታውም የእሱ ንብረት ነበር፡፡ እሳቸው ቦታውን የኃይማኖት ማዕከል ካደረጉት በኋላ የእሱ ስም እንዳይረሳ፣ የእሱ ስም ከእሳቸው ስም ጋር ተደርቦ 'ድሬ ሼኽ ሁሴን' እንዲባል በማዘዛቸው ነው፡፡ እነዚህ ሁለት መላምቶች እንዳሉ ሆነው፣ የድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ ሰፊ ሜዳማ ስፍራ ላይ የሚገኝ ሲሆን፣ መሰል ሜዳማ ስፍራዎችን 'ድሬ' በሚል መሰየም በአካባቢው የተለመደ ነው፡፡ ይህ ደግሞ ድሬ ሼኽ ሁሴን የሚለው ስያሜ የሼኽ ሁሴን ሜዳማ መሬት ከሚለው መነሻ ያደረገ እንደሆነ መረዳት ያስችላል፡፡

'አናጂና' ሌላው የአካባቢው ስም ነው፡፡ ሼኽ ሁሴን በሕይወት በነበሩበት ወቅት በአካባቢው ጂኒዎች (ሰይጣኖች) በብዛት ይኖሩ ነበር ይባላል፡፡ በአንድ ወቅት ሼኽ ሁሴን በአካባቢው ሲንቀሳቀሱ ጂኒውን ያገኙትና 'አንተ ማን ነህ?' ብለው ሲጠይቁት 'አና ጂን' አላቸው፡፡ በአረብኛ 'አና ጂን' ማለት 'እኔ ጂኒ ነኝ' ማለት ነው፡፡ ከዛን ጊዜ ጀምሮ ስፍራው አናጂና እንደተባለ ይነገራል፡፡ በአካባቢው በብዛት የነበሩ ጂኒዎችም በሼኽ ሁሴን ጸሎት አማካኝነት ከአካባቢው መራቃቸው ይነገራል፡፡ በአሁኑ ወቅት አናጂና የሚለው ስያሜ መካነ ቅርሱ የሚገኝበት ቀበሌ ስም በመሆን እያገለገለ ይገኛል፡፡

'ቢርካ' የአካባቢው ሌላው ስም ነው፡፡ ይህ የስፍራው ስያሜ እምብዛም የተለመደ ባይሆንም፣ አልፎ አልፎ የአካባቢው ነዋሪዎች ሲጠቀሙበት ይስተዋላል፡፡ ቢርካ የአረብኛ ቃል ሲሆን ትርጉሙም ውኃ የሚጠራቀምበት ቦታ (ኩሬ) ማለት ነው፡፡ ቢርካ፣ ሼኽ ሁሴን አዘውትረው ይቀመጡበት የነበረ የቦታ ስያሜን መነሻ ያደረገ ነው፡፡

### 4.2 የቅዱስነት እሳቤ እና አዕምሯዊ ውክልና

በአዕምሯዊ ካርታ አስተሳሰብ ከኃይማኖት ጋር በተገናኘ አንድ መልክዓምድር ቅዱስ ስፍራ የሚባለው አራት መስፈርቶችን ሲያሟላ እንደሆነ Eliade (1959፣37) ይገልጻል፡፡ እነሱም፡- አንደኛ፣ ስፍራው የቃልኪዳን፣ የሕግ፣ የልዩ መለኮታዊ ትዕዛዝ ወይም መሰል አይነት ስምምነት (A break) ያለው ሲሆን፤ ሁለተኛ፣ ይህ ስምምነት ከአንዱ የሕዋ ክበብ (Cosmic region) ወደ ሌላ የሕዋ ክበብ (ከመሬት ወደ ገነት ወይም ከገነት ወደ መሬት ወይም ከመሬት ወደ መሬት በታች) የሚያገናኝ ትዕምርት ያለው ሲሆን፤ ሶስተኛ፣ ከገነት ጋር የሚኖርን ተግባቦት በአንድ ወይም ከዛ በላይ በሆኑ ምልክቶች የሚገልጽ ሲሆን እና አራተኛ፣ በስፍራው በሚገኝ የሕዋ ነጥብ (Cosmic axis) ዙሪያ ዓለም መኖሯና ነጥቡ የዓለም ማዕከል ሲሆን ነው፡፡

ድሬ "በፈጣሪ የተመረጠ ቅዱስ ስፍራ" እንደሆነ በሼኽ ሁሴን ተከታዮች ዘንድ ይታመናል፡፡ ይህ እምነት በስፍራው ተፈጽመዋል ተብለው የሚነገሩና የሚታመኑ የታጋይ ሚቶችን (Hero myths) መሰረት ያደረገ ነው፡፡ የታጋይ ሚቶች በተለያዩ ሀይማኖቶችና እምነቶች ውስጥ ለሀይማኖቱ መመስረት፣ ማደግ ወይም የማህበረሰቡን ችግሮች ለመፍታት ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያላቸው ግለሰቦች ወይም መንፈሳዊ አካላት በሕይወት ዘመናቸው የፈጸሙትን መስዋዕት፣ ገድል ወይም ተዓምር የሚገልጹ ናቸው (Campbell 2004 [1949])፡፡

ሼኽ ሁሴን ፈጽመዋቸዋል ተብለው የሚታመኑና የሚነገሩ የታጋይ ሚቶች በርካታ ናቸው፡፡ ከእነዚህ መካከል ከመካነ ቅርሱ መገኛ ቦታ ጋር የሚገናኙት ሁለት ናቸው፡፡ አንደኛው፤ የሼኽ ሁሴን እናት ነፍሰጡር ሆነው በአናጂና ሲያልፉ "አላህ እዚህ ተወለድ ብሎኛል፤ የእኔ ስፍራ እዚህ ስለሆነ ልወለድ!" ብለው በማህጸን ውስጥ እያሉ እናታቸውን መጠየቃቸውን የሚገልጽ ነው፡፡ ሌላው፤ በአንጻሩ ሼኽ ሁሴን በተወለዱበት ወቅት ከሰማይ ብርሃን ወርዶ፣ ጭለማውን እንዳበራና አካባቢው በብርሃን ጸዳል እንደተሞላ የሚገልጽ ነው፡፡

ሼኽ ሁሴን ሲወለዱ ብርሃን እንደወረደላቸው በመታመኑም ምክንያት "ኑር ሁሴን" በሚል ስያሜ ይጠራሉ፡፡ በአረብኛ 'ኑር' ማለት ብርሃን ሲሆን፤ "ኑር ሁሴን" ብርሃናማው ሁሴን ማለት ነው፡፡ ሁሴን በአረብኛ የሰው ስም መጠሪያ ሲሆን፤ ትርጉሙም የተወደደ፣ የተመረጠ፣ የተመረቀ ማለት ነው፡፡ የእሳቸው የመጠሪያ ስም ያለው ትርጓሜና ሲወለዱ ብርሃን ከሰማይ እንደወረደላቸው መታመኑ የቦታውንና የሼኽ ሁሴንን ቅድስና ተዓማኒነት ለማጽናት አስተዋጽኦ አበርክቷል፡፡

ድሬ፣ ሼኽ ሁሴን የተወለዱበት፣ ያደጉበት፣ ሀይማኖታዊ ትምህርት ያስተማሩበት፣ ቤተሰብ መስርተው ወግ ማዕረግ ያዩበትና ረጅም ጊዜ በጸሎት የቆዩበት ስፍራ እንደሆነ ይታመናል፡፡ በመሆኑም የእሳቸው መለኮታዊ ኃይል (Divine power) ከሌሎች ቦታዎች በተለየ እዚህ ስፍራ ላይ አለ ብለው ተከታዮቻቸው ያምናሉ፡፡ እነዚህ እምነቶች ድሬን ሼኽ ሁሴን እንዲወለዱበት፣ እንዲያድጉበት፣ እንዲያስተምሩበት፣ ተዓምራትን እንዲፈጽሙበት፣ ለሰው ልጅ ሁሉ መዳኛ እንዲሆን የተመረጠ፣ ለአርባ አመታት በፆም በፀሎት የቆዩበትና ብርሃን ከሰማይ የወረደበት ቅዱስ ስፍራ መሆኑን ያሳያሉ፡፡ በመሆኑም ስፍራው የቅዱስነትና በልዩ የመመረጥ እሳቤ ይዟል፡፡ ይህ እሳቤ ፈጣሪ መዲናን ለነብዩ መሐመድ፣ የሲናን ተራራ ለነብዩ ሙሴ፣ ቤተልሔምን ለኢየሱስ ክርስቶስ እንደመረጠ ሁሉ፣ ድሬንም ለሼኽ ሁሴን መምረጡን ያሳያል፡፡

ድሬ "የበረከት፣ የፈውስና የንጽህና ማግኛና መመረጥን ማረጋገጫ ስፍራ" እንደሆነ ይታመናል፡፡ የሼኽ ሁሴን ተከታዮች ካለባቸው የኢኮኖሚ፣ የጤና፣ የማህበራዊ ሕይወትና መሰል ችግሮች ለመፈወስ፣ ልጅ ያጡትም ለማግኘት፣ በሕይወታቸው በረከት ለማግኘት፣ ከምድራዊ ሕይወት በኋላ ነፍሳቸው በገነት እንድትኖርና የወደፊት ምኞታቸው እንዲሳካ በሚል ወደ ስፍራው ይሄዳሉ፡፡ ስፍራው ላይ በመድረሳቸውም ያሰቡት ሁሉ እንደሚሳካ በሙሉ ልባቸው ያምናሉ፡፡

በሼኽ ሁሴን ተከታዮች ዘንድ ድሬን የሚረግጥ ሰው በሼኽ ሁሴን የተመረጠና የተፈቀደለት ብቻ ነው ተብሎ ይታመናል፡፡ በመሆኑም ማንኛውም ሰው ለሙዳ በዓላት ወይም ለሌላ ምክንያት ወደ ድሬ መሄድ ስለፈለገ ብቻ ተነስቶ አይሄድም፡፡ 'ሙዳ' በድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ የሚከበሩ 'የኢድ-አል-አድሃ' እና 'ዛህራ ገልገላ ኀበና' በዓላት ጥቅል መጠሪያ ነው፡፡ 'ሙዳ'፤ የሚለው ቃል የኦሮምኛ ቃል ሲሆን፣ በስፍራው የሚከበሩ በዓላትን ከመግለጹ በተጨማሪ፣ በበዓላቱ ወቅት የሚከወኑ ስርዓቶችን፣ ወደ ስፍራው የሚደረግ መንፈሳዊ ጉዞን እንዲሁም ወደ ስፍራው መንፈሳዊ ጉዞ የሚያደርግን ተጓዥ የሚገልጽ ነው፡፡ በመካነ ቅርሱ የሚከበሩት የኢድ-አል-አድሃ እና የዛህራ ገልገላ ኀበና የሙዳ በዓላት እያንዳንዳቸው እስከ 10 ቀናት የሚሸፍኑ ደማቅ ኃይማኖታዊ በዓላት ናቸው፡፡

ግለሰቦች በራሳቸው ፍላጎት መሰረት ለሙዳ በዓላት ወደ ድሬ ለመሄድ ዝግጅት ሊያደርጉ ይችላሉ፡፡ ይሁን እንጂ ወደ ስፍራው እንዲሄዱ የሼኽ ሁሴን ፍቃድ ከሌለ ወደ ስፍራው ማንም መሄድ እንደማይችል ይታመናል፡፡ የሼኽ ሁሴን ፍቃድ ከሌለ በትራንስፖርት እጦት፣ በገንዘብ እጦት፣ በጤና እጦት፣ በመርሳት ወይም በሌሎች የተለያዩ ምክንያቶች ሰበብ ሆነው ጉዞው ይደናቀፋል ተብሎ ይታመናል፡፡ ወደ ድሬ ለመሄድ

የሼኽ ሁሴን ፍቃድ እንደሚያስፈልግ ሁሉ፣ ለመቅረትም የእሳቸው ፍቃድ አስፈላጊ ነው ተብሎ ይታመናል፡፡ የእሳቸው ተከታዮች በሙዳ በዓላት ወቅት በተለያዩ ምክንያቶች ወደ ድሬ ላለመሄድ ይወስናሉ፡፡ ወይም መሄድ ፈልገው በትራንስፖርት፣ በገንዘብ ወይም ስፍራውን ባለማወቅ ለመቅረት ይወስናሉ፡፡ የእነዚህ ግለሰቦች የድሬ ጉዞ በሼኽ ሁሴን ዘንድ ተቀባይነት ካገኘና ከተፈለገ በምንም ምክንያት ከጉዟቸው ሊቀሩ አይችሉም ተብሎ ይታመናል፡፡

ድሬ "የተለያዩ መንፈሶች የሚመጡበት ስፍራ" ነው፡፡ በድሬ የተለያዩ መንፈሶች እንደሚመጡ ይታመናል፡፡ መንፈሶቹ የሚመጡት በሁለት ባህርያዊ መንገዶች ነው፡፡ እነሱም፣ በመንፈስና እንደ ሰው በአካል ናቸው፡፡ በስፍራው ሼኽ ሁሴን በመንፈስና በአካል ይመጣሉ ተብሎ የሚታመን ሲሆን በመንፈሳዊ ጸጋቸው የበቁ ናቸው የሚባሉ ግለሰቦች ሼኽ ሁሴንን በመንፈስ እንዳዩ ይናገራሉ፡፡ ሼኽ ሁሴን በመንፈስ በሚታዩበት ወቅት በጣም ነጭና የሚያንጸባርቅ ልብስ የለበሱ ሽማግሌ መስለው እንደሆነ ይናገራሉ፡፡ ሼኽ ሁሴን ከመንፈስ በተጨማሪ የሰው ስጋ ለብሰው እንደ ሰው በአካል ይመጣሉ ተብሎ ይታመናል፡፡ እሳቸውም እንደ ሰው በአካል በመምጣት መልዕክት ይናገራሉ፣ ያስጠነቅቃሉ፣ እርዳታ ይጠይቃሉ፣ ያበረታታሉ ተብሎ ይታመናል፡፡

በድሬ በመንፈስ ባህርይ ይመጣሉ ተብለው የሚታመኑ መንፈሶች አሉ፡፡ እነዚህ መንፈሶች "ሮሃኒያ" በሚል ስያሜ ይጠራሉ፡፡ ሮሃኒያ የሚለው ቃል አረብኛ ሲሆን ትርጉሙም፤ በዐይን የማይታይ ረቂቅ ፍጡር ማለት ነው፡፡ ሮሃኒያዎች ሰው ጠልፈው ይወስዳሉ ተብሎ ይታመናል፡፡ የወሰዱትንም ሰው ለሚፈልጉት ጊዜ ያህል እነሱ ዘንድ አቆይተው ይመልሱታል ወይም በዛው እንደወሰዱት ያስቀሩታል ተብሎ ይታመናል፡፡

## 4.3 የንጽጽር እሳቤ እና አዕምሯዊ ውክልና

በአዕምሯዊ ካርታ አስተሳሰብ መሰረት በመልክዓምድር ላይ የሚኖር አዕምሯዊ ውክልና ከሚፈጠርባቸው ሂደቶች አንዱ "እሳቤያዊ የውክልና ስዕል" ነው፡፡ ይህ የውክልና ስዕል የሚፈጠረው ደግሞ በአዕምሮ ውስጥ ባሉ የተለያዩ መረጃዎች መካከል ንጽጽር በመፍጠር እንደሆነ Ardalan እና Bakhtiar (1973፣13) Corbin (1960)ን ጠቅሰው ገልጸዋል፡፡ ይህን መሰል ንጽጽር በድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስና በሳዑዲ አረቢያው-መካ መካከል ይስተዋላል፡፡

ለኢድ-አል-አድሃ (አረፋ) በዓል ወደ ሳዑዲ አረብያ መካ የሚደረግ የሐጅ መንፈሳዊ ጉዞ አለ፡፡ የሐጅ መንፈሳዊ ጉዞ በዱል-አል-ሒጃ ወር በ8ኛው ቀን የሚጀምር ሲሆን፣ ለ6 ተከታታይ ቀናት የሚከወን ነው (Gulevich 2004)፡፡ በተመሳሳይም በዚህ በዓል ወቅት ወደ ድሬ ሼኽ ሁሴን መንፈሳዊ ጉዞ

ይደረጋል፡፡ በመካነ ቅርሱ በመቶ ሺሕ የሚቆጠር ሕዝብ በስፍራው በመገኘት በዓሉን በደማቅ ሁኔታ ያከብራሉ፡፡

በድሬ ሼኽ ሁሴን ለኢድ-አል-አድሃ (አረፋ) በዓል በርካታ ቁጥር ያለው ህዝብ ለአምልኮ የሚሄድበትና ከመካ ጋር ተመሳሳይ ተደርጎ የሚታሰብ በመሆኑ ይመስላል Braukämper (2004) መካነ ቅርሱን የ"ሰሜን ምስራቅ አፍሪካ መካ" በሚል የገለጸው፡፡ የድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስን የ"ደሃ ሰው ሐጅ" በሚል Cerulli (1941) መግለጹን Eshetu (1973፣24) ጠቅሷል፡፡ በተመሳሳይም Baxter (1987) መካነ ቅርሱ የ"ደሃ ሰው መካ" መሆኑን የሚያንጸባርቁ የቃል ግጥሞች እንዳገኘ ይገልጻል፡፡

የ"ደሃ ሰው መካ" የሚለው አስተሳሰብ ወደ ድሬ ሼኽ ሁሴን የሚሄደው አብዛኛው ሰው በቂ ገንዘብ የሌለው በመሆኑ፣ እንዲሁም ሀብታም ሰው ወደ መካ ሲሄድ፣ ደሃው ወደ ድሬ ይሄዳል ከሚል አረዳድ የመጣ ይመስላል፡፡ እንደ አብዛኛው የኢትዮጵያ ሕዝብ የሼኽ ሁሴን ተከታዮችም በአነስተኛ የኢኮኖሚ ደረጃ ላይ የሚገኙ ናቸው፡፡ በመሆኑም አባባሉ በአንድ መልኩ ትክክል ይመስላል፡፡ ነገር ግን እጅግ ሐብታም የሆኑ ጥቂት የሼኽ ሁሴን ተከታዮች የግል ሂሊኮፕተር ይዘው፣ ሐብታም የሆኑ በርካቶች ደግሞ የግል መኪናቸውን ይዘው ወደ ስፍራው እንደሚመጡ በቦታው በተደረገው የመስክ ምልከታ ለመታዘብ ተችሏል፡፡ ይህ ደግሞ ጉዳዩን ሙሉ በሙሉ ከኢኮኖሚ አቅም ጋር ማያያዝ እንደማይቻል አመላካች ነው፡፡

በድሬ ሼኽ ሁሴን ከአካላዊና ከአዕምሯዊ ሕመሞች ለመፈወስ የሚያገለግል ዘምዘም አለ፡፡ ዘምዘም የአረብኛ ቃል ሲሆን ትርጉሙ ጸበል ማለት ነው፡፡ ይህ ዘምዘም መንፈሳዊ ተጓዦች ከተለያዩ ሕመሞች እንፈወስበታለን ብለው በማመናቸው በመጠጣት፣ በመታጠብና በመረጨት ይጠቀሙበታል፡፡ በተመሳሳይም በመካ ዘምዘም አለ፡፡ ዘምዘም በሁለቱም ስፍራዎች በመገኘቱ ስፍራዎቹ እንዲመሳሰሉ ምክንያት ሆኗል፡፡

በድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ ጀዋራ አለ፡፡ ጀዋራ ለመድኃኒትነት የሚያገለግል ቅዱስ አፈር እንደሆነ ይታመናል፡፡ የጀዋራ አፈር አመድማ መልክ ያለው ሲሆን፣ ሲቀመስ የጥፍጥና ባህሪ አለው፡፡ የጀዋራ ቅዱስ አፈር ማንኛውንም ሕመም እንደሚፈውስና ክፉ መናፍስትን እንደሚያባርር ይታመናል፡፡ አማኞቹ የጀዋራ አፈርን በመብላት፣ ሰውነትን በመቀባት፣ በዘምዘም በመበጥበጥና በሌሎች የተለያዩ መንገዶች ይጠቀሙበታል፡፡ በሳዑዲ አረቢያ-መካ የሚገኝ አፈር ቅዱስ እንደሆነ ይታመናል፡፡ መንፈሳዊ ተጓዦችም ቅዱሱን አፈር ለመድኃኒትነት ይጠቀሙበታል፡፡

ከእነዚህ በተጨማሪ በድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስና በመካ መካከል ተመሳስሎ እንዲኖርና፣ ሁለቱ ስፍራዎች ተቀራራቢ መንፈሳዊ ዋጋ ያላቸው ተደርጎ እንዲታመን ምክንያት የሆኑ ጉዳዮች አሉ፡፡ እነዚህ ጉዳዮችም መንፈሳዊ ተጓዦች ከተለያዩ ዓለማት ለሐጅ ወደ ድሬ መሄዳቸው፣ ስፍራው ቅዱስ እንደሆነ መታመኑ፣ በስፍራው ነብዩ መሐመድ በመንፈስ እንደመጡ መታመኑ፣ ሼኽ ሁሴን ከመካ እንዳመጡት የሚታመነውና "ደራራ በሹ" በሚል ስያሜ የሚታወቅ ጥቁር ድንጋይ መኖር፣ ነብዩ መሐመድ ሼኽ ሁሴንን ለመጎብኘት በመንፈስ እንደመጡ መነገሩ፣ ከድሬ እስከ መካ የሚያደርስ ዋሻ እንዳለና በዋሻውም ሼኽ ሁሴን መካ እንደሄዱ መታመኑ ናቸው፡፡

## 4.4 የሁሉምነት እሳቤ እና አዕምሯዊ ውክልና

Punkhurst (1994) በኢትዮጵያ ውስጥ በሚገኙ አስር ቦታዎች ከሚካሄዱ መንፈሳዊ ጉዞዎች በመነሳት ጉዞዎቹ ያላቸውን ባህርይ በአራት ይመድባቸዋል፡፡ እነሱም፣ የአንድ ብሔር አባላት ብቻ የሚሄዱበት፣ የተለያየ ብሔር ያላቸው ሰዎች በአንድ የሚሄዱበት፣ የፖለቲካ ድንበርን (የዓለም አቀፍ ወይም የአገር ድንበርን) በመሻገር የሚሄዱበት፣ የተለያየ ኃይማኖት ያላቸው ሰዎች በአንድ የሚሄዱበት ናቸው፡፡ የተለያየ ኃይማኖት፣ ብሔርና ቋንቋ ያላቸውና የኃይማኖትና የብሔር ድንበርን እንዲሁም ዓለም አቀፍና አገራዊ ድንበርን በመሻገር ግለሰቦች በጋራ መንፈሳዊ ጉዞ ከሚያደርጉባቸው ቅዱስ ስፍራዎች መካከል አንዱ የድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ መሆኑን Punkhurst (1994፣939) ይገልጻል፡፡

ወደ ድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ የእስልምና፣ የክርስትና የዋቄፈና እና የሌላ ኃይማኖት ተከታዮች ለአምልኮ ይሄዳሉ፡፡ በመሆኑም ድሬ "የሰው ልጅን በአንድ ስፍራ የሚያገናኝ" ነው፡፡ በሙዳ በዓላት ወቅት የሼኽ ሁሴን ተከታዮች በኢትዮጵያ ውስጥ ከሚገኙ የተለያዩ አካባቢዎች እንዲሁም በአሜሪካ፣ በአውሮፓና በሌሎችም የዓለም አገራት የሚገኙ ኢትዮጵያውን በመካነ ቅርሱ ይገኛሉ፡፡ ከኢትዮጵያውያን በተጨማሪ የሱማሌ፣ የኬንያ፣ የጅቡቲ፣ የየመን፣ የኢራንና የሳውዲ አረቢያ ዜጎች በዓሉን ለማክበር ይመጣሉ፡፡ ለበዓሉ የተለያየ ብሔር ተወላጆችም ይገኛሉ፡፡ በድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ የሚከበሩት የሙዳ በዓላት ከተለያዩ አካባቢዎች፣ አገሮች፣ ብሔሮችና ሀይማኖቶች የመጡ ሰዎች የሚገኙባቸው በመሆኑ በሀገራችን  በእስልምና፣ በክርስትና ወይም በሌሎች ሀይማኖቶች ውስጥ ከሚገኙ ስርዓተከበራ (ritual) መፈጸሚያ ስፍራዎች መካነ ቅርሱን ልዩ ያደርገዋል፡፡

ድሬ ሼኽ ሁሴን የተለያዩ የዓለም ሕዝቦችን፣ የሀገራችን ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦችን፣ እንዲሁም የተለያዩ ኃይማኖቶች ተከታይ የሆኑ

ሕዝቦችን በአንድ የሚያገናኝ ነው። ከኢትዮጵያ የተለያዩ የማህበረሰብ ክፍሎች ወደ መካነ ቅርሱ ስለሚሄዱ Eliyas (2012፤19) ስፍራውን "ትንሿ ኢትዮጵያ" ብሎ ገልጾታል። ድሬ ሼኽ ሁሴን "አንድነት በልዩነት ውስጥ" የሚንጸባረቅበትና ከተለያዩ የዓለም ሀገራት መንፈሳዊ ጉዞ የሚያካሂዱበት የሀገራችን ልዩ ስፍራ በመሆኑ "ትንሿ ዓለም" ተብሎ ሊገለጽ ይችላል።

Eliade (1959፤37) የአንድ መልክዓምድር የቅዱስ ስፍራነት መስፈርቶች ብሎ ከገለጻቸው መካከል አንዱ ስፍራው የቃልኪዳን፣ የሕግ፣ የልዩ መለኮታዊ ትዕዛዝ ወይም መሰል አይነት ስምምነት ያለው መሆኑ ነው። በሼኽ ሁሴን ተከታዮች ዘንድ ድሬ፣ የሼኽ ሁሴን መንፈስ የሚገኝበት በመሆኑ የታመመ የሚድንበት፣ ንብረት ያጣ የሚያገኝበት፣ ልጅ ያጣ የሚያገኝበት ቅዱስ ስፍራ እንደሆነ ይታመናል። ስፍራው እሳቸው እንዲወለዱበት፣ እንዲያስተምሩበትና ተዓምራትን እንዲፈጽሙበት በፈጣሪ የተመረጠ ነው ተብሎ ይታመናል።

ይህ ደግሞ በሼኽ ሁሴን ተከታዮች ዘንድ ድሬ ለሰው ልጅ መድህን እንዲሆን ፈጣሪ በቃልኪዳን የመረጠው ልዩ ስፍራ እንዲሆን ምክንያት ሆኗል። ከኃይማኖት አንጻር መልክዓምድር በራሱ የቅዱሳን መገኛ ተደርጎ ስለሚታመን የኃይል ስበት ማዕከል (Fields of force) እንደሆነ Fickeler (1962፤97) ይገልጻል። እነዚህ ሁነቶች ድሬ የመለኮታዊ ትዕዛዝ፣ የቃል ኪዳን ስምምነት ያለው እንዲሁም የመለኮታዊ ኃይል የስበት ማዕከል ተደርጎ እንዲታመን አስችለዋል።

## 4.5 ሰው ሰራሽ ግንባታዎች እና አዕምሯዊ ውክልና

ድሬ "የሼኽ ሁሴን መካነ መቃብር የሚገኝበት" እንደሆነ ይታመናል። የሼኽ ሁሴን ተከታዮች የእሳቸው አጽም በመካነ ቅርሱ ቅጽር ግቢ ውስጥ እንዳረፈ ያምናሉ። ይህም እምነት ስፍራው የተቀደሰ፣ የሼኽ ሁሴን መንፈስ ያረፈበት ተደርጎ እንዲታሰብ አስችሏል። አጽማቸው ባረፈበት ቦታም በሼኽ ሁሴን ስም የተገነባ 'ገሞ' አለ። 'ገሞ' የኦሮምኛ ቃል ሲሆን፣ ትርጉሙም ሕንጻ ማለት ነው። ገሞ በአረብኛ 'ቁባ' በሚል ይጠራል።

የሼኽ ሁሴን ገሞ በተገነባበት ቦታ የእሳቸው አጽም መኖር፣ አለመኖሩ በግልጽ አይታወቅም። ነገር ግን የእሳቸው የመቃብር ስፍራ ገሞው የተሰራበት ቦታ ላይ ወይም እዛው አካባቢ እንደሆነ ይታመናል። የእሳቸው መቃብር በእሳቸው ስም ከተገነባው ገሞ አርባ ሜትር ርቀት ላይ ተመስጥሮ እንደሚገኝ መሐመድ ሼኽ ሁሴን (ዓ.ም የለውም፤6) ጠቅሶ፣ መቃብሩ እንዳይታወቅ ምስጢር ከተደረጉበት ምክንያቶች አንደኛው፣ በወቅቱ በሌላ አካባቢ የሚኖሩ የኑር ሁሴን አፍቃሪዎች አስክሬኑን አውጥተው እንዳይወስዱ የሚል ሲሆን፣ ሁለተኛው ደግሞ ፈሪሃ-አላህ

ያላደረባቸው ሰዎች በመካነ መቃብራቸው ላይ ቆመው እንዳይረጋገሙበት ተሰግቶ እንደሆነ ያስረዳል፡፡

ከእነዚህ ሁለት ምክንያቶች በተጨማሪ የእሳቸው አስክሬን የት እንዳረፈ በትክክል እንዳይታወቅ ያደረገው ሌላኛው ምክንያት እሳቸው ከዚህ ዓለም በተለዩበት ወቅት የተፈጠረው ክስተት መሆኑን መረጃ ሰጪዎች ይገልጻሉ፡፡ ይህም በእሳቸው የሕልፈት እለት ከአናጂና ወደ ሌላ ስፍራ መርዶ ሲላክ፣ ከሌላ አካባቢም በተመሳሳይ የሼኽ ሁሴን ሕልፈትን የሚገልጽ መርዶ ወደ አናጂና ይላክ ነበር፡፡ በወቅቱም በተለያዩ ቦታዎች ‘ሁሴን’ በሚል ስም የሚታወቁ በርካታ ሰዎች ሕይወታቸው አልፎ እንደነበር ይነገራል፡፡

ይህም ልዩ ክስተት ሁሉም በየአካባቢው “የሼኽ ሁሴን የመቃብር ስፍራ እዚህ ነው” በሚል የመታሰቢያ ገሞ እንዲገነባ ምክንያት ሆኗል፡፡ ለዚህም ይመስላል በእሳቸው ስም የተገነቡ ገሞዎች በተለያዩ የአገሪቷ ስፍራዎች ያሉት፡፡ ከእነዚህ ስፍራዎች መካከል በአርሲ ዞን በአርባጉጉ፣ በኮፈሌ፣ በሺርካና በሰኪና ወረዳዎች፣ በባሌ ዞን በመደወላቡ ወረዳ እና በምስራቅ ሐረርጌ ዞን በጨርጨር ወረዳ የሚገኙት ይጠቀሳሉ፡፡

ድሬ በተለያዩ ወቅቶች ወደ ስፍራው የመጡ የኃይማኖት አባቶች አጽም ያረፈበት መካነ መቃብር የሚገኝበት ነው፡፡ አጽማቸው ባረፈበት ስፍራም የመታሰቢያ ገሞዎች ተገንብተዋል፡፡ በመካነ ቅርሱ ከሚገኙት አስር ገሞዎች መካከል ዘጠኙ የመቃብር ስፍራዎች ናቸው፡፡ የቅዱሳን መካነ መቃብርን መነሻ አድርገው የተመሰረቱ መንደሮች በተለያዩ የዓለም ክፍሎች አሉ፡፡ እነዚህ መንደሮች “ኒክሮፖሊስ” (Necropolises) በሚል ስያሜ ይጠራሉ፡፡ መካነ ቅርሱ የሚገኝበት የአናጂና መንደር የተመሰረተውም የሼኽ ሁሴን እና የሌሎች ቅዱሳን አባቶች መካነ መቃብርን መነሻ አድርጎ ነው፡፡ በመሆኑም አናጂና በአገራችን ውስጥ ከተመሰረቱ መሰል ኒክሮፖሊስ መንደሮች መካከል አንዱ ነው፡፡

በኃይማኖት አንድን መልክዓምድራዊ ስፍራ ቅዱስ ከሚያሰኙት አራት መስፈርቶች መካከል አንደኛው ስፍራው ያለው የቃልኪዳን ስምምነት ከአንዱ የሕዋ ክበብ ወደ ሌላ የሕዋ ክበብ (ከመሬት ወደ ገነት ወይም ከገነት ወደ መሬት ወይም ከመሬት ወደ መሬት በታች) የሚያገኛኝ ትዕምርት ያለው እንደሆነ Eliade (1959፣37) ይገልጻል፡፡ በድሬ የፈጣሪ ቃልኪዳን ስምምነት መኖሩን ከሚገልጹ ግንባታዎች መካከል አንዱ የሼኽ ሁሴን ገሞ ነው፡፡

የሼኽ ሁሴን ገሞ በድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ ከሚገኙ 10 ገሞዎች መካከል ረጅም እድሜ ያለው ነው፡፡ ገሞው የ375 አመት እድሜ እንዳለው

የድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ ባህልና ቱሪዝም ጽ/ቤት ሪፖርት (2002 ዓ.ም፣2) ይገልጻል። የሼኽ ሁሴን ገሞ የሚገኘው በግንብ በታጠረው ቅጽር ግቢ መሃል ላይ በሚገኝ ተጨማሪ የግምብ አጥር ውስጥ ነው። ገሞው በኪነ-ህንጻ ዲዛይኑና ትልቀቱ በአካባቢው ከሚገኙ ሌሎች ገሞዎች የተለየ ያደርገዋል። ገሞው 45 ሜትር ርዝመት፣ 35 ሜትር ስፋትና 3 ሜትር ከፍታ አለው (Hailemelekot እና Mulugeta 2015፣28)።

የሼኽ ሁሴን ገሞ መንፈሳዊ ተጓዦች በስፍራው እንደደረሱ የሚዘይሩት (የሚጎበኙት) ነው። የታመመ እንዲድን፣ ልጅ ያጣ እንዲወልድ፣ የተቸገረ እንዲያገኝ ስለት የሚሳልበትና የሚለምንበት ነው። የሼኽ ሁሴን ገሞ መንፈሳዊ ተጓዦችን ከፈጣሪ ጋር የሚያገናኝ ነው። የሼኽ ሁሴን ወዳጆችን ከሼኽ ሁሴን መንፈስ ጋር የሚያገናኝ ነው። መንፈሳዊ ተጓዦችን ከአናጂና መንደር ነዋሪዎች ጋር የሚያስተሳስር ነው። በመሆኑም የሼኽ ሁሴን ገሞ ራሱን ማዕከል በማድረግ ግለሰብን፣ ማህበረሰብን፣ ሼኽ ሁሴንን እና ፈጣሪን በአንድ ቦታ ያገናኛል። ገሞው በእነዚህ አራት አካላት መካከል የአራትዮሽ ትስስር (Rectangular relationship) ይፈጥራል። ይህ የአራትዮሽ ትስስር የሼኽ ሁሴን ገሞ በተጨባጩ ዓለምና በማይጨበጠው ምናባዊ ዓለም (Metaphysical) መካከል ሕብር (Harmony) የመፍጠር ሚና እንዲኖረው ምክንያት ሆኗል።



ፎቶ 1፤ የሼኽ ሁሴን ገሞ (ፎቶ በአጥኚዎች፣ 2008 ዓ.ም)

የሼኽ ሁሴን ገሞ የሚገኘው በመካነ ቅርሱ መሃል ላይ ነው። ይህም ገሞው የመካነ ቅርሱ እምብርት እንዲሆን አስችሎታል። በፎቶግራፉ ላይ እንሚታየው ገሞው የመርከብ ቅርጽ አለው። መርከብ መጓጓዣ ነው።

ምድር በውኃ በተዋጠችበት ዘመን ፍጡራን የዳኑት በኖህ መርከብ ነው፡፡ የኖህ መርከብ በእስልምናና በክርስትና ኃይማኖቶች የመዳን ተምሳሌት ነው፡፡ የሼኽ ሁሴን ገሞም አማኞች ከክፉ ነገር የሚድኑበት፣ በመንፈስ ከፍ የሚሉበት፣ ዘራቸውንና ተስፋቸውን የሚያስቀጥሉበት የመርከብ ተምሳሌት ነው፡፡ ይህ የኪነህንጻ ዲዛይኑ የመካነ ቅርሱ እምብርት የመሆኑ ተጨማሪ ማሳያ ነው፡፡

የሼኽ ሁሴን ገሞ መሬትን ከሰማየሰማያት ጋር የሚያገናኝ ነው፡፡ በገሞው አናት ላይ ወደ ሰማይ የወጣ ቀስት መሰል ጉጥ አለ፡፡ ይህ ቀስት መሰል ጉጥ ምድርን ከሕዋ ጋር የሚያገናኝ ነው፡፡ በጉጡም ምክንያት ሕዋን ወደ ምድር ይስባል፤ ምድርንም ወደ ሕዋ ይወስዳል፡፡ ከገሞው ስር የሼኽ ሁሴን አጽም ይገኛል ተብሎ ይታመናል፡፡ በመሆኑም ገሞው ሶስት አካላትን በአንድ አገናኝቶ የያዘ ነው፡፡ ሰማይን፣ መሬትንና ከመሬት በታች ያለን አካል፡፡ ይህ ሚናውም ገሞው በመሬት ላይ የሚገኝ የሕዋ እምብርት (Center of the universe) እንዲሆን አስችሎታል፡፡

ገሞው ባለው የሕዋ እምብርትነትም የማህበረሰቡን ኃይማኖታዊ፣ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊና ስነልቡናዊ ሁነቶችን የመቅረጽ፣ የመወሰንና የመግለጽ ሚና አለው፡፡ ከዚህ አንጻር ገሞው ያለውን እሳቤያዊ ውክልና (Archetype) ስንመለከት ቅዱስነቱን፣ መንፈሳዊ ቅቡልነቱን (Eternal felicity)፣ መንፈሳዊ ፍርድ ሰጪነቱን፣ ምድርን ከሰማየሰማይ ጋር አገናኝነቱን፣ ሕዋ ተሻጋሪነቱን (Cosmic transcendence)፣ ተዓምራት ፈጻሚነቱንና የማህበረሰቡን ሁለንተናዊ ማንነት ወሳኝነቱን ያመላክታል፡፡

አንድ መልክዓምድር ቅዱስ ከሚያስብሉት አራት መስፈርቶች መካከል አንዱ በስፍራው በሚገኝ የሕዋ ነጥብ (Cosmic axis) ዙሪያ የዓለም መኖርና ነጥቡ የዓለም ማዕከል መሆኑ ነው (Eliade 1959)። በሼኽ ሁሴን ገሞ አማካኝነት ሰው ከሰው ጋር፣ ሰው ከሼኽ ሁሴን ጋር፣ ሰው ከፈጣሪው ጋር እንዲሁም ሰው ከገነት ጋር ይገናኛል፡፡ በዚህም ባህሪው የምድር የሕዋ ክበብን ከሰማየሰማይ የሕዋ ክበብ ጋር ያገናኛል፡፡ የሼኽ ሁሴን ገሞ የሕዋ ነጥብ በመሆን ምድርን ከገነት ጋር፣ ሰውን ከረቂቅ መንፈስ ጋር የሚያገናኝ ነው፡፡ በመሆኑም ስፍራው የህዋ ነጥብንና የዓለም ስርዓትን አቅፎ የያዘ የዓለም ማዕከል እንደሆነ ያሳያል፡፡

ድሬ ከመቃብር ስፍራነቱም በተጨማሪ የሼኽ አብድ-አል-ቃዲር አል-ጀይላኒ (በድሬና አካባቢው አጠራር ሼኽ አብዱልቃድር ጀይላኒ) ከኢራቅ ባግዳድ ወደ ስፍራው በመጡበት ወቅት ድንኳናቸውን ጥለው ተቀምጠውበታል በሚባለው ስፍራ በእሳቸው ስም የተገነባ ገሞ አለ፡፡ ሼኽ አብድ-አል-ቃዲር አል-ጀይላኒ እ.አ.አ በ1077 በኢራቅ አገር ጊለን (ኪለን) በምትባል ከተማ ተወልደው እስከ 1166 የኖሩ የኃይማኖት ፍልስፍና ሊቅ ናቸው

(ሙሐመድ ዐሊ፣ ዓ.ም የለውም፣2)። ሼኽ አብዱልቃድር በእስልምና ኃይማኖት ታሪክ ውስጥ ትልቅ ተጽዕኖ የፈጠረውን የቃድሪያ ስርዓት መስራች ናቸው። የቃድሪያ ስርዓት በሱፊዝም ታሪክ የመጀመሪያው መደበኛ አስተምህሮ ነው (Renard, 2009፣19)።

በድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ 15 መስጂዶች አሉ። ይህን ያህል በርካታ ቁጥር ያላቸው መስጂዶች በአንድ ስፍራ መገኘት በሀገራችን በሚገኙ መሰል የአምልኮ ስፍራዎች ዘንድ እምብዛም የተለመደ አይመስልም። በመካነ ቅርሱ ከ900 ዓመት በላይ ያስቆጠሩት የባላና የዙቅጡም መስጂዶች ይገኛሉ። የባላ መስጂድ ሼኽ ሁሴን በመካነ ቅርሱ ያስገነቡት የመጀመሪያው መስጂድ እንደሆነ ይነገራል። የባላ መስጂድ መቼ እንደተገነባ የተለያዩ መረጃዎች አሉ። የባላ መስጂድ ከተገነባ 971 አመት እንደሆነው የድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ ባ/ቱ/ጽ/ቤት ሪፖርት (2002 ዓ.ም፣2) ይገልጻል። Abinet (2011፣52) የ935 ዓመት እድሜ እንዳለው ሲገልጽ፣ Østebo (2012፣52) ደግሞ እ.አ.አ በ1067 ተገነባ ይላል። ዙቅጡም ከባላ መስጂድ ቀጥሎ በሼኽ ሁሴን የተሰራ እንደሆነ ይነገራል። የዙቅጡም መስጂድ ከተገነባ 944 አመት እንደሆነው የድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ ባ/ቱ/ጽ/ቤት ሪፖርት (2002 ዓ.ም፣2) ይገልጻል። መስጂዱ በአሁኑ ወቅት አገልግሎት በመስጠት ላይ ይገኛል።

በድሬ ሼኽ ሁሴን 9 ሰው ሰራሽ የውኃ ኩሬዎች አሉ። ከእነዚህ ኩሬዎች መካከል ረጅም እድሜ ያስቆጠሩት ‘ሀሮ ቁራ’ እና ‘ሀሮ ሉኩ’ ናቸው። እነዚህ ሁለት የውኃ ኩሬዎች ሼኽ ሁሴን እራሳቸው እንደገነቧቸው ይነገራል። ‘ሀሮ’ በኦሮምኛ ኩሬ ማለት ነው። ‘ሀሮ ቁራ’፣ የቁራ ኩሬ የሚል ትርጉም አለው። የውኃ ኩሬው የሚገኘው በባላ መስጂድ አጠገብ ነው። ኩሬው ከባላ መስጂድ ጋር አብሮ እንደተገነባ ይነገራል። ሀሮ ቁራ በአሁኑ ወቅት ምንም አይነት አገልግሎት አይሰጥም። ይህ ጥንታዊ ሰው ሰራሽ የውኃ ኩሬ ከተገነባ 981 አመት እንደሆነው ይነገራል።

ከሀሮ ቁራ ቀጥሎ የተገነባው ሀሮ ሉኩ ነው። ‘ሀሮ ሉኩ’፣ የዶሮ ኩሬ የሚል ትርጉም አለው። ሀሮ ሉኩ የ958 አመት እድሜ እንዳለው የድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ ባ/ቱ/ጽ/ቤት ሪፖርት (2002፣3) ይገልጻል። የሀሮ ሉኩ የውኃ ኩሬ 8 ሜትር አማካይ ጥልቀት እንዳለው ይገመታል። ኩሬው ሼኽ ሁሴን እራሳቸው ያስቆፈሩት እንደሆነ ይነገራል። ሀሮ ሉኩ በዙሪያው በታጠረው ቅጽር ግቢ ውስጥ የሚገኝ ብቸኛ የውኃ ኩሬ ነው።

ሀሮ ሉኩ ለዘምዘምነት (ለጸበልነት) ብቻ የሚያገለግል በመሆኑ በመካነ ቅርሱ ከሚገኙ ሌሎች የውኃ ኩሬዎች የተለየ መንፈሳዊ ዋጋ አለው። የሼኽ ሁሴን ተከታዮች የሀሮ ሉኩ ዘምዘምን በመጠጣት፣ አካላቸውን

በመታጠብና በመረጨት ካለባቸው አካላዊና አዕምሯዊ ሕመም እንፈወሳለን ብለው ያምናሉ፡፡ በመካነ ቅርሱ የሀሮ ሉኩ ዘምዘም መኖሩ ስፍራው ልዩ መንፈሳዊ ዋጋ ያለው፣ ፈጣሪ ለሰው ልጅ መድህን ይሆን ዘንድ ባርኮ የሰጠው ዘምዘም (ጸበል) መገኛ፣ የፈጣሪ ቃልኪዳን ማረጋገጫ ምልክት ያረፈበት እንዲሁም ፈጣሪ፣ ሼኽ ሁሴንና የሰው ልጅ ጥብቅ ቁርኝት የፈጠሩበት ስፍራ ተደርጎ እንዲታመን ምክንያት ሆኗል፡፡

## 4.6 ተፈጥሯዊ ገጽታዎች እና አዕምሯዊ ውክልና

መልክዓምድራዊ ሁነቶች በራሳቸው የኃይማኖትን እሳቤ የሚቀርጹ፣ የሚገልጹና የሚይዙ ልዩ ምልክቶች እንደሆኑ Eliade (1959) ይገልጻል፡፡ በመሆኑም በአንድ አካባቢ የሚገኙ (ተራራ፣ ወንዝ፣ ሜዳ፣ የአየር ጸባይ፣ ዋሻ የመሳሰሉት) ተፈጥሮዎች በመልክዓምድር ላይ የሚኖረንን እሳቤ የሚቀርጹ ናቸው፡፡ በዚህ ባህርያቸውም መልዕክት ያስተላልፋሉ፡፡ በመልክዓምድር ላይ ከሚገኙ ተፈጥሯዊ ሁነቶች መነሻነት የድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ ያለውን አዕምሯዊ ውክልና ቀጥለን እንመልከት፡፡

የድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ በአራት ወንዞች የተከበበ ነው፡፡ መካነ ቅርሱን በሰሜን የዋቤ ሸበሌ፣ በደቡብ የኤጀ ጉራቲ፣ በምስራቅ የቀቀለም እና በምዕራብ የበሀራ ወንዞች ያዋስኑታል፡፡ በአራት ወንዞች መከበብ የሰማያዊው ጀነት (ገነት) ምልክት ነው፡፡ በቅዱስ ቁርዓን (ኢብራሂም፤ 14÷23) ጀነት የወተት፣ የወይን፣ የማር እና የፍራፍሬ የተሰኙ አራት ወንዞች የሚመነጩበት እንደሆነ ይገልጻል፡፡ በመጽሐፍ ቅዱስ (ኦሪት ዘፍ. 2÷10-15) ከገነትም ፊሶን፣ ግዮን፣ ጢግሮስ እና ኤፍራጥስ የተሰኙ አራት ወንዞች እንደሚመነጩ ይገልጻል፡፡

በመካነ ቅርሱ ክልል ውስጥ ሶስት ወንዞች ያልፉበታል፡፡ ወንዞቹም የአይናገኜ፣ የቆርጋ እና የጂና ወንዝ ናቸው፡፡ እነዚህ ወንዞች መካነ ቅርሱን የውኃ ሀብት ማዕከል አድርገውታል፡፡ ይህ ደግሞ በጀነት ያለውን የውኃ ሀብት ለመግለጽ ቅዱስ ቁርዓን (ሱራ፤56÷31) ‘‘የውኃ መግነጢሳዊ ስሜት’’ (“Gushing water”) ያለው ከሚለው ስፍራ ጋር ይመሳሰላል፡፡ መካነ ቅርሱ ለሼኽ ሁሴን ተከታዮች ልዩ የውኃ መግነጢሳዊ ስሜትን የሚሰጥና ሰማያዊውን የጀነት ቅርጽ በምድር ላይ የያዘ ነው፡፡ ይህ የጀነት አምሳያ (Replica) በምድር ላይ የማስቀመጥ አንድምታዊ እሳቤ በሼኽ ሁሴን ተከታዮች ዘንድ መካነ ቅርሱ እንደ ጀነት የተቀደሰ ተደርጎ እንዲታሰብ ምክንያት ሆኗል፡፡

በመካነ ቅርሱ የአይናገኜ ዋሻ ይገኛል፡፡ ዋሻው ከዋናው የግምብ አጥር በግምት 3 ኪ.ሜትር ርቀት ላይ ይገኛል፡፡ በዋሻው ውስጥ ሼኽ ሁሴን ለአርባ ዓመታት ያህል በጸሎት መቆየታቸው ይነገራል፡፡ እሳቸው በዋሻው በቆዩባቸው አመታት የተለያዩ ተዓምራትን ማድረጋቸው ይነገራል፡፡

ከእነዚህ ተዓምራዊ ድርጊቶች መካከል ለአርባ ዓመታት ያህል ግንባራቸውን እሾህ እንዲወጋው አድርገው መስገዳቸው፣ ለአርባ ዓመታት ያህል የዱር ቅጠል እየበሉ፣ ጨው በውኃ በጥብጠው እየጠጡ በዋሻው ውስጥ በሚኖሩበት ወቅት እሳቸውን ሊበሉ የመጡ እንስሳትን ረግመው ወደ ድንጋይ መቀየራቸው ይጠቀሳሉ፡፡ በእርግማኑ ምክንያት እንስሳቱ ወደ ድንጋይ መቀየራቸውን የሚያጸኑ በዋሻ ውስጥ የእባብ፣ የአዞና የዘንዶ ቅርጽ ያላቸው የሚመስሉ ግን ምንነታቸውን መለየት የሚያዳግቱ የድንጋይ ቅርጾች ይገኛሉ፡፡



ፎቶ 2፣ በአይናገኜ ዋሻ ውስጥ የሚገኙና የአውሬ ቅርጽ ያላቸው የሚመስሉ ድንጋዮች፡፡ (ፎቶ በአጥኚዎች፣2009 ዓ.ም)፡፡

ከላይ በፎቶ ግራፉ ላይ የሚታዩትና በአይናገኜ ዋሻ ውስጥ የሚገኙት የድንጋይ ቅርጾች በቅርበት ሲታዩ የደረቀ አውሬ ይመስላሉ፡፡ አይናገኜ የሚለው ስያሜ የምን ቋንቋ ቃል እንደሆነና ትርጉሙ ምን ማለት እንደሆነ ማግኘት አልተቻለም፡፡ ይሁንና በቅዱስ ቁርዓን ውስጥ "አይናኒያ" የሚል ቃል አለ፡፡ አይናኒያ፣ ወደ ሲኦል መግቢያ ድልድይ ነው፡፡ ይህ ድልድይ በእባብ ይመሰላል፡፡ ከዚህ መረጃ አይናኒያ በእባብ የሚመሰል ድልድይ ወይም እባብ ያለበት የሲኦል መግቢያ ነው ማለት ነው፡፡

በድሬ ሼኽ ሁሴን የሚገኘው አይናገኜ ዋሻ ስያሜ "አይናኒያ" ከሚለው የአረብኛ ቃል የመጣ ይመስላል፡፡ ምክንያቱም በአይናገኜ ዋሻ መግቢያው ላይ ወደ ድንጋይነት ተቀይረው ነው ተብለው የሚታመኑ እባብ መሰል ቅርጾች ይገኛሉ፡፡ ዋሻውን የሲኦል ወካይ አድርጎ በመውሰድ፤ ልክ እንደ

አይናኒያ በሲያል መግቢያ ላይ እንዳለ የእባብ ድልድይ በአይናገኜ መግቢያ ላይም እባብ መሰል ቅርጾች አሉ፡፡ በሼኽ ሁሴን ተከታዮች ዘንድ ስፍራው በምድር ላይ ያለ የሲያል መግቢያ በር አምሳያ ተደርጎ እንዲታሰብ አስችሎታል፡፡

ከአይናገኜ ዋሻ በቅርብ ርቀት ላይ የአይናገኜ ገደል አለ፡፡ ሼኽ ሁሴን በዚህ ገደል ውስጥ ከሰው ተሰውረው የዱር ቅጠሎችን እየተመገቡና ጨው በውኃ በጥብጠው እየጠጡ ለአርባ አመታት ያህል በጸሎት መቆየታቸው ይነገራል፡፡ ገደል ከአረብኛው "ካውታሃር" ከሚለው ቃል ትርጓሜ ጋር ይቀራረባል፡፡ "ካውታሃር" ወይም ገደል የጀነት (ገነት) መግቢያ ደጃፍ ውክልና ነው፡፡ እንደ Smith እና Haddad (1981፣80) አገላለጽ በነባር የእስልምና ባህል እሳቤ ገደል ጀነት ከመግባት በፊት እራስን የማጽጃ፣ የመቀደሻና ንስኃ የመቀበያ ስፍራ ተደርጎ ይወሰዳል፡፡ ሼኽ ሁሴንም በሕይወታቸው ፍጻሜ አቅራቢያ ለአርባ ዓመታት ያህል በአይናገኜ ገደል ውስጥ የኖሩት ወደ ጀነት ከመግባታቸው በፊት እራሳቸውን ለማጽዳት፣ ለመቀደስና ንስኃ ለመቀበል እንደሆነ ይታመናል፡፡ ይህም በሼኽ ሁሴን ተከታዮች ዘንድ ስፍራው በምድር ላይ ያለ የገነት መግቢያ በር አምሳያ ተደርጎ እንዲሳል ምክንያት ሆኗል፡፡

የድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ በባሌ ሰንሰለታማ ተራሮችና በዋቤ ሸበሌ ሸለቆ መካከል የሚገኝ ሜዳማ ስፍራ ነው፡፡ መካነ ቅርሱ ዙሪያው በአራት ተራራዎች የተከበበ ነው፡፡ ተራራዎቹም፣ ደደላ፣ቀጨም ሳሬ፣ አበል ቃሲም እና ኩባዩ በሚል ስያሜ ይጠራሉ፡፡ በተራራዎች መከበብ የምድር ተምሳሌት ነው፡፡ በእስልምና ኃይማኖት ነገረ ፍጥረት (Cosmology) እሳቤ ምድር በሁለት ተራራዎች የተከበበች ነች፡፡ ይህ ምድር በተራራ የመከበብ እሳቤ "ቃፍ" ይባላል፡፡ በተመሳሳይም በክርስትና ነገረ ፍጥረት እሳቤ ምድር በሁለት ተራራዎች የተከበበች ነች፡፡ ከምድር በምስራቅ አቅጣጫ አድማስ እና በምዕራብ አቅጣጫ ናጌብ የተሰኙ ሁለት ተራራዎች አሉ፡፡

ፀሐይ በምድር ላይ በምስራቅ አቅጣጫ በአድማስ ተራራ አናት ላይ ወጥታ፣ በምዕራብ አቅጣጫ በናጌብ ተራራ ስር ትጠልቃለች፡፡ በድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስም ፀሐይ በምስራቅ አቅጣጫ በሚገኘው የአበል ቃሲም ተራራ አናት ላይ ወጥታ፣ በምዕራብ አቅጣጫ በሚገኘው የደደላ ተራራ አናት ስር ትጠልቃለች፡፡ ይህም የድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ ከምድር ጋራ ያለውን ተመሳስሎ ያሳያል፡፡ የመካነ ቅርሱ በተራራ መከበብ በሼኽ ሁሴን ተከታዮች የነገረ ፍጥረት እሳቤ ስፍራው የምድር ተምሳሌት ተደርጎ እንዲታሰብ አድርጎታል፡፡

ምድር የፍጡራን መኖሪያ ብቸኛ ፕላኔት እንደሆነች ሁሉ፣ የሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስም የፍጡራን ሁሉ የጋራ መሰብሰቢያና መዳኛ ስፍራ ነው፡፡

ይህ የምድር ተምሳሌትነትም በሼኽ ሁሴን ተከታዮች አዕምሮ ውስጥ ስፍራው ልዩ መለኮታዊ ኃይል ያለው፣ የተቀደሰና በፈጣሪ የተመረጠ ተደርጎ የተቀረጸ እሳቤያዊ ውክልና (Archetype) እንዲኖረው አስችሏል፡፡

መልክዓምድር ልዩ አዕምሯዊ ካርታ የሚይዘው የማይታየውን ህዋዊ ዓለም፣ ከሚታየው ተጨባጭ ዓለም ጋር በኮግኒቲቭ በማገናኘት ነው፡፡ በኮግኒቲቭ የማገናኘት ሂደቶች መካከል "ምናባዊ ቁስ አካል" ወደ "እሳቤያዊ የውክልና ስዕል" መቀየር እንደሆነ Ardalan እና Bakhtiar (1973፣10) Corbin (1960)ን ጠቅሰው ገልጸዋል፡፡ በዚህ ሂደት መሰረት የሼኽ ሁሴን ተከታዮች አዕምሮ ውስጥ ያለውና በቅዱስ መጻሕፍት የተገለፁትን ምናባዊ የጀነት፣ የጀነት መግቢያ በር፣ የሲዖል መግቢያ በር እሳቤዎች ወደ ሚታየውና ተጨባጭ ወደ ሆነው የመካነ ቅርሱ መልክዓምድራዊ ገጽታ እንዲቀየር አስችሏል፡፡

## 4.7 የሼኽ ሁሴን ባህርያት እና የመካነ ቅርሱ እሳቤያዊ ትስስር

በተከታዮቻቸው ዘንድ ሼኽ ሁሴን በርካታ ባህርያት አሏቸው ተብሎ ይታመናል፡፡ ከእነዚህ ባህርያት መካከል አንዱ "የአባትነት" ባህርይ ነው፡፡ "ሼኽ ሁሴን የፍጡራን ሁሉ አባት ናቸው፡፡" ተብሎ ይታመናል፡፡ በሼኽ ሁሴን ዘንድ የሰው ልጅ ሁሉ እኩል ነው፡፡ የሰው ልጅ በኃይማኖት፣ በዘር፣ በጾታ፣ በእድሜ፣ በማህበራዊ፣ በኢኮኖሚ፣ በስልጣን፣ በአካባቢ፣ በአገርና በአሕጉር ደረጃ ያለው ልዩነት በእሳቸው ዘንድ ቦታ የለውም፡፡ እሳቸው ሁሉንም በአንድ ዐይን የሚያዩ፣ የሁሉም አባት ናቸው፡፡ የሼኽ ሁሴን አባትነት ለሰው ልጆች ብቻ ሳይሆን ለእንስሳት፣ ለእጸዋት፣ ለግዑዝ አካላትና ለረቂቅ ፍጡራን ጭምር እንደሆነ በተከታዮቻቸው ዘንድ ይታመናል፡፡

በተለያዩ ኃይማኖቶች አስተምህሮ እስካሁን ወደ ምድር የመጡ መንፈሳዊያን የራሳቸው ልዩ ልዩ ጸጋዎች አሏቸው፡፡ በጸጋቸውም በአካባቢያቸው ወይም በዓለም አቀፍ ደረጃ ከፍተኛ ተጽዕኖ ፈጥረዋል፡፡ ሁሉም መንፈሳዊያን የራሳቸው ተልዕኮና ጸጋ እንዳላቸው ሁሉ ሼኽ ሁሴንም የራሳቸው ተልዕኮና ጸጋ አላቸው ተብሎ ይታመናል፡፡ የሼኽ ሁሴን ተልዕኮ ለሰው ልጅና ለሌሎችም ፍጡራን ነው፡፡ ጸጋቸውም ፍጡራንን ሁሉ ማዳን፣ ከክፉ ነገር መጠበቅ፣ ፍጡራንን ሁሉ ያለ አድሎ በእኩል ዐይን ማየት እንደሆነ ተከታዮቻቸው ያምናሉ፡፡

በዚህ እምነት መሰረት "ሼኽ ሁሴን የሁሉም፤ ሁሉም የሼኽ ሁሴን" ነው፡፡ ይህ የሁሉምነትን ባህሪያዊ እሳቤ Gadamer (1976) "ጥሪ" ("Adressing") በሚል ይገልጸዋል፡፡ Gadamer (1976) ጥሪ የሚለውን እሳቤ ሲያብራራ መንገድ ላይ ስንሄድ የአዛን (አላህን የማወደስ ወይም የመጥራት ዜማ) ድምጽ ስንሰማ ጥሪው ለእስልምና ኃይማኖት ተከታዮች ነው፡፡ የኃይማኖቱ

ተከታዮችም የአዛኑ ድምጽ ይጠራቸዋል፤ ምክንያቱም እነሱን ስለሚመለከት፡፡ ከእስልምና ኃይማኖት ውጪ ያለ ግለሰብ የአዛኑን ድምጽ ምናልባትም ሙሉ ለሙሉ ላይሰማ ይችላል፡፡ ጽምጹን ቢሰማም ጥሪው ለእሱ ስላልሆነ ልቡ አይደነግጥም፡፡ በክርስትናውም የቤተክርስቲያን ደወል ወይም ቅዳሴ ተመሳሳይ ነው፡፡

በGadamer (1976) እሳቤ የሼኽ ሁሴን ጥሪ የሚደርሰው ለሁሉም ፍጡር ነው፡፡ ለሰው ልጅም፣ ለእንሰሳትም፣ ለአጸዋትም ጭምር፡፡ የእሳቸው ጥሪ ለሁሉም ኃይማኖት ተከታይ ነው፡፡ ጥሪው ለሙስሊሙም፣ ለክርስቲያኑም፣ ለዋቄፈታውም … ለሁሉም ነው፡፡ ይህ የሼኽ ሁሴን ባህርይ ሁሉን አቃፊ፣ ሁሉን ሰብሳቢ፣ ሁሉን ጠባቂ ያደርጋቸዋል፡፡ ለሼኽ ሁሴን ሁሉም የ"እኛ" እንጂ "የእኛ እና የእነሱ" አይነት አስተሳሰብ የለም፡፡ ይህ እሳቤ ፍጡር ሁሉ የሼኽ ሁሴን ነው፤ ሼኽ ሁሴንም የሁሉ ፍጡር ነው የሚል እምነት በተከታዮቻቸው ዘንድ ጥልቅ መሰረት እንዲኖረው አድርጓል፡፡

ይህ ባህሪያቸውም ሼኽ ሁሴን የአብሮነት፣ የእኩልነት፣ የጋራነት እና የእኛነት ባለ ድል (champion) ያደርጋቸዋል፡፡ ሼኽ ሁሴን አቃፊ፣ ደጋፊና ሰብሳቢ ናቸው እንጂ ገፊና አግላይ አይደሉም ተብሎ እንደሚታመነው ሁሉ፤ የሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስም የሁሉም ነው ተብሎ ይታመናል፡፡ ይህም ወደ መካነ ቅርሱ የሚሄድ ሰው ሁሉ በስፍራው ሲደርስ ነጻነት ይሰማዋል፤ የእኔነት ስሜት ይሰማዋል እንጂ የባይተዋርነት፣ የመገለልና የመነጠል ስሜት አይሰማውም የሚል ጽኑ እምነት ፈጥሯል፡፡

ተከታዮቻቸው መካነ ቅርሱ አለው ብለው ከሚያምኗቸው እነዚህ ባህርያት ሼኽ ሁሴንም አላቸው ተብሎ የሚታመኑት "የአባትነት"፣ "የሁሉምነት"፣ "የእኩልነት"፣ "የእኛነት" ባህሪያዊ እሳቤዎች፣ ጋር ተመሳሳይ ነው፡፡ በመሆኑም ሼኽ ሁሴን የመካነ ቅርሱ፣ መካነ ቅርሱ ደግሞ፤ የሼኽ ሁሴን አምሳያዊ ነጸብራቅ ሆኗል፡፡ "ሰው ቦታን ይቀድሳል፤ ቦታ ደግሞ በምላሹ ሰውየውን ይዘክረዋል፡፡" እንደሚባለው ሼኽ ሁሴን የመካነ ቅርሱን ባህርይ ቀራጭ፤ መካነ ቅርሱም የሼኽ ሁሴን ዘካሪና የማንነት ነጸብራቅ እንዲሆን አስችሎታል፡፡

## 5. ማጠቃለያ

"የአዕምሯዊ ካርታ" በኮግኒቲቭ ንድፈሃሳብ ስር የሚመደብ አስተሳሰብ ነው። በዚህ አስተሳሰብ መሰረት መልክዓምድር በሰው አዕምሮ ውስጥ ልዩ ትርጉም፣ ውክልና፣ ዋጋና መልዕክት አለው። መልክዓምድር የተለየ መልዕክት የሚኖረው በቦታው የሚገኙ ልዩ ልዩ ምልክቶችን በአዕምሮ ውስጥ በማስገባት ትርጉም ሲይዙና የጋራ ማህበራዊ እሳቤዎች ሲፈጥሩ ነው። ይህ ጥናት "የአዕምሯዊ ካርታ" አስተሳሰብን መሰረት በማድረግ የሼኽ ሁሴን ተከታዮች፣ በድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ ላይ ያላቸውን መልክዓምድራዊ እሳቤ ከአዕምሯዊ ውክልና አንጻር ምን መልክ እንዳለው ለማሳየት ሞክሯል።

ጥናቱ የድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ የተቀደሰ፣ ልዩ መንፈሳዊ ኃይል ያለው፣ በፈጣሪ የተመረጠ፣ በስፍራው መገኘትም መመረጥን የሚያረጋግጥ እንደሆነ መታመኑን ያሳያል። ይህ የቦታው ልዩ ዋጋና ውክልና መሰረት ያደረገው የቦታው ስያሜ፣ በቦታው ላይ የሚነገሩ አፈ-ታሪኮች፣ የሼኽ ሁሴን ተከታዮች ያላቸው የጋራ ግንዛቤ፣ ዕይታና ልምድ እንደሆነ ጥናቱ ያሳያል።

በኃይማኖት ስርዓት ውስጥ አንድ መልክዓምድር ቅዱስ የሚባለው አራት መስፈርቶችን ሲያሟላ ነው። እነሱም፤ አንድ፤ ስፍራው የቃልኪዳን፣ የሕግ፣ የልዩ መለኮታዊ ትዕዛዝ ወይም መሰል አይነት ስምምነት ያለው ሲሆን፣ ሁለት፤ ይህ ስምምነት ከአንዱ የሕዋ ክበብ ወደ ሌላ የሕዋ ክበብ የሚያገኛኝ ትዕምርት ያለው ሲሆን፤ ሶስት፤ ከገነት ጋር የሚኖርን ተግባቦት በአንድ ወይም ከዛ በላይ በሆኑ ምልክቶች የሚገልጽ ሲሆን፣ አራት፤ በስፍራው በሚገኝ የሕዋ ነጥብ ዙሪያ የዓለም መኖርና ነጥቡ የዓለም ማዕከል መሆኑ ናቸው። ይህ ጥናት በእነዚህ አራት የቅድስና መስፈርቶች መነሻነት የድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስን ገጽታ አሳይቷል።

ድሬ፣ ሼኽ ሁሴን እንዲወለዱበት ቀድሞ በፈጣሪ የቃልኪዳን ስምምነት መሰረት የተመረጠ፣ እሳቸውም የተወለዱበት፣ ያደጉበት፣ የተማሩበት፣ ያስተማሩበት፣ ልዩ ልዩ ተዓምራት የፈጸሙበት፣ የኃይማኖት ሊቃውንትን የተቀበሉበት፣ አርባ አመት በጸሎት የቆዩበት፣ አጽማቸው ያረፈበት፣ መንፈሳዊ ኃይላቸው ያለበት እንዲሁም ለዘለዓለም ለሰው ልጅ መድህን እንዲሆን የመረጡት ቅዱስ ስፍራ እንደሆነ የእሳቸው ተከታዮች እንደሚያምኑ ጥናቱ ያሳያል።

በተከታዮቻቸው እምነት ድሬ በአምላክ ምርጫ የተመሰረተ፣ የምድር እምብርት ወይም የሕዋ ማዕከል በመሆኑ የሰው ልጅ ከአምላኩ ጋር የሚገናኝበት ነው። መካነ ቅርሱ ወደ ስፍራው መንፈሳዊ ጉዞ የሚያደርግ ግለሰብን፣ በአካባቢው የሚኖር ማህበረሰብን፣ ሼኽ ሁሴንንና ፈጣሪን

በአንድ በማገናኘት የአራትዮሽ የግንኙነት ትስስር እንዲፈጠር ምክንያት ሆኗል፡፡ በመካነ ቅርሱ የሚገኘው የሼኽ ሁሴን ገሞ ምድርን፣ ከምድር በታች ያለን አካል እንዲሁም ከምድር በላይ ያለን አካል በአንድ በማገናኘት የሶስትዮሽ ትስስር በመፍጠር በተጨባጩ ዓለምና በምናባዊ ዓለም መካከል ሕብር እንዲኖር ማድረጉን ጥናቱ ያሳያል፡፡

መካነ ቅርሱ የሚገኝበት ስፍራ በአራት ተራራዎች የተከበበ መሆኑ የምድር ተምሳሌት፤ በአራት ወንዞች የተከበበ መሆኑ ደግሞ የጀነት (የገነት) ቅርጽ ያለውና በምድር ላይ ያለ የገነት አምሳያ፣ የአይናገኜ ገደል የገነት መግቢያ በር እንዲሁም የአይናገኜ ዋሻ የሲኦል መግቢያ በር ተደርጎ እንዲታሰብ ምክንያት ሆኗል፡፡ በዚህ ሚናውም ስፍራው የመንፈስ ኃይል የስበት ማዕከልና የዓለምን ስርዓት አቅፎ የያዘ የሕዋ እምብርት እንዲሆን ማስቻሉን ጥናቱ ያሳያል፡፡ በተከታዮቻቸው ዘንድ ሼኽ ሁሴን አላቸው ተብሎ የሚታመኑት "የአባትነት"፣ "የሁሉምነት"፣ "የእኩልነት"፣ "የእኛነት" ባህርያዊ እሳቤዎች፣ መካነ ቅርሱ አለው ብለው ከሚያምኑት መገለጫ ጋር ተመሳሳይ ነው፡፡ በመሆኑም ሼኽ ሁሴን የመካነ ቅርሱ፣ መካነ ቅርሱ ደግሞ፤ የሼኽ ሁሴን አምሳያ ተደርጎ እንደሚታሰብ ጥናቱ አሳይቷል፡፡

## ዋቢ ጽሑፎች

መሐመድ ሼህ ሁሴን ዳውድ፡፡ ዓ.ም የለውም፡፡ *አሳሁመ-እርሐም ሼክና ሁሴን ቁጥበል-ሐበሹ፡* ሐዋሳ፡፡

*መጽሐፍ ቅዱስ፤ አዲሱ መደበኛ ትርጉም፡፡* 1993 ዓ.ም፡፡ አዲስ አበባ፣ ኢንተርናሽናል መጽሐፍ ቅዱስ ማህበር፡፡

ሙሐመድ ዐሊ፡፡ ዓ.ም የለውም፡፡ *ሸይኽ ዐብዱልቃድር ጂላኒ፡፡* አዲስ አበባ፤ ነጃሺ ማተሚያ ቤት፡፡

ቅዱስ ቁርኣን፡፡ 1997 ዓ.ም፡፡ ሁለተኛ እትም፡፡ ነጃሺ አሳታሚ ድርጅት፡፡

የድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ ባህልና ቱሪዝም ጽህፈት ቤት፡፡ 2002 ዓ.ም፡፡ "በድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ የሚገኙ ኪነ-ህንጻዎች ታሪክ፡፡" (ያልታተመ)፡፡

ፈቃደ አዘዘ፡፡ 1991፡፡ *የሥነ-ቃል መምሪያ፡፡* አዲስ አበባ፤ ቦሌ ማተሚያ ድርጅት፡፡

Abinet Eshete. 2011. "Impacts of Pilgrimage Tourism: The Case of Bale Dire Sheikh Hussein." (Unpublished M.A Thesis), Department of Archeology and Heritage Management, Addis Ababa University.

Andresen, J. 2001. *Religion in Mind: Cognitive Perspectives on Religious Belief, Ritual and Experience*. Cambridge University Press

Andrzejewski, B. 1972. "Allusive Diction in Galla Hymns in Praise of Sheikh Hussien of Bale." *The School of Oriental and African Studies,* African Language Studies XIII.

_______. 1975. "A Genealogical Note Relevant to the Dating of Sheikh Hussein of Bale." *Bulletin of the School of Oriental and African Studies 38*. (1). PP 139-40.

Areba Abdella, Abel Gezahegn & Ibrahim Kaso. 2003. "Dirre Sheik Hussien Shrine to be Inscribe in the Regional, National and World Heritage List." (Unpublished), Bale Robe: Bale Zone Culture and Tourism Office.

Ardalan, N. & Bakhtiar, L. 1973. *The Sense of Unity: the Sufi Tradition in Persian Architecture*. University of Chicago Press.

Baxter, P. 1987. "Some Observations on the Short Hymns Sung in Praise of Sheikh Nur Hussein of Bale." In Ahmed al-Shahi (Ed), *The Diversity of the Muslim Community:*

*Anthropological Essays in Memory of Peter Lienhardt,* PP 139-152.

Beit-Hallahmi, B & Argyle, M. 1997. *The Psychology of Religious Behavior, Belief and Experience.* New York: Routledge.

Bloor, M. & Wood F. 2006. *Keywords in Qualitative Methods: A Vocabulary of Research Concepts*. London: SAGE Publications.

Braukämper, U. 2004. *Islamic History and Culture in Southern Ethiopia: Collected Essays*. London: LIT Publishers.

Campbell, J. 2004 [1949]. *The Hero with A Thousand Faces*. New York: Princeton University Press.

Cerulli, E. 1922. "The Folk-Literature of the Galla of Southern Abyssinia." *In Harvard African Studies, Varia Africa 3*, PP 9-22.

Eliade, M. 1959. *The Sacred and the Profane: the Nature of Religion*. Translated by Willard R., New York: Harcourt Brace & Co.

Eliyas Teha. 2012. "Understanding Rituals and Analyzing Songs Performed at Dirre Sheikh Hussein." (Unpublished M.A Thesis), Department of Social Anthropology, Addis Ababa University.

Eshetu Setegn. 1973. "Shaikh Hussayn of Bale and His Followers." (Unpublished Senior Essay), Department of History, Faculty of Art, Haile Selassie I University.

Francaviglia, R. 2003. *Believing in Place: A Spritual Geography of the Great Basin.* University of Nevada Press.

Fickeler, P. 1962. "Fundamental Question in the Geography of Religion." in *Readings in Cultural Geography*, University of Chicago Press: Chicago.

Gadamer, H. 1976. *Philosophical Hermeneutics*. Translated by David E. Linge; University of California Press: Los Angeles.

Gemechu Geda. 2013. "Pilgrimages and Syncretism: Religious Transformation among the Arsi Oromo of Ethiopia." (Unpublished PhD Dissertation), University of Bayreuth, Faculty of Cultural Studies, Germany.

Goldstein, K. 1964. *A Guide for Field Workers in Folklore*. Detroit: Gale Research Company.

Gulevich, T. 2004. *Understanding Islam and Muslim Traditions: An Introduction to the Religious Practices, Celebrations, Festivals, Observances, Beliefs, Folklore, Customs, and Calendar System of the World's Muslim Communities, Including an Overview of Islamic History and Geography*. Michigan; Omnigraphics, Inc.

Hailemelekot Agizew & Mulugeta Abegaz. 2015. "The Dirre Sheikh Hussein Religious, Cultural and Historical Heritage Site Management Plan." (Unpublished), Authority for Research and Conservation of Cultural Heritage, Addis Ababa.

Isaac, E. 1959. "Religion Landscape and Space." *In Landscape Journal, 9*.(2) PP 14-18).

Kothari, R. 2004. *Research Methodology*. New Delhi: New Age International Publisher.

Lewis, I. 1977. "The Western Somalia Liberation Front (WSLF) and the Legacy of Sheikh Hussein of Bale." *Proceeding of the fifth International Conference of Ethiopa: Nice*.

McCauley, N. 2010. *Cognition, Religious Ritual, and Archaeology*. Queen's University Belfast Press.

Mohamed Hassen. 1990. *The Oromo of Ethiopia:* A History 1570-1860. Cambridge University Press.

Østebo, T. 2012. *Localising Salafism: Religious Change among Oromo Muslims in Bale, Ethiopia.* Boston: Brill NV Publications.

Punkhurst, Alula. 1994. "Reflections on Pilgrimage in Ethiopia." New Trends in Ethiopian Studies: *In Proceeding of the 12th International Conference of Ethiopian Studies.* Edited by Harold G. Marcus, and *et al* PP 933- 953, New Jersey: Red Sea Press INC.

Renard, J. 2009. *The A to Z of Sufism.* N0, 44, UK: The Scarecrow Press.

Smith, D. 1896. "Expeditions through Somaliland to Lake Rudolf". *in Geographical Journal*. London.

Smith, J. & Haddad, Y. 1981. *The Islamic Understanding of Death and Resurrection*. Albany: State University of New York.

Sperber, D. 1990. "The Epidemiology of Beliefs." *In The social; Psychoogical Study of Widespread Beliefs*. Franser C. and Gaskell G. (Eds). PP 25-44, Oxford: Clarendon Press.

Staeheli, A. & Mitchell, D. 2007. *Locating the Public in Research and Practice*. Institute of Geography. Edinburgh; University of Edinburgh.

Temam Haji-Adam. 2002. "Islam in Arsi, Southeast Ethiopia (Ca, 1840-1974)." (Unpublished M.A Thesis), Addis Ababa University.